
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማእከል ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥና የአቅም ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት








መጋቢት 2011

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ..... i
ድርሞ..... I
/Executive Summery/..... I
ክፍል አንድ ..... 1
መግቢያ ..... 1
የማዕከሉ አመሰራረት ..... 2
የማዕከሉ ራዕይ ..... 2
ተልዕኮ..... 2
የማዕከሉ የተሸሻሉ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት..... 2
የማዕከሉ ተገልጋዮች፣ ባለ ድርሻ አካላትና ተባባሪዎች ..... 4
ተገልጋዮች ..... 4
ባለ ድርሻ አካላት ..... 4
የማዕከሉ አደረጃጀት እና የሰው ሀይል ..... 7
የሰው ኃይል ..... 7
የፋይናንስ ምንጭ፡- ..... 8
የማዕከሉ አሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description) ፡- ..... 9
የኦዲቱ ዓላማ፡- ..... 11
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ..... 11
የኦዲቱ ወሰን ..... 11
የኦዲቱ ዘዴ ..... 11
የኦዲት አከባቢ..... 11
የኦዲትየትኩረት አቅጣጫወች እና የኦዲት መመዘኛ መስፍርት..... 12
የኦዲትየትኩረት አቅጣጫወች..... 12
የኦዲት መመዘኛ መስፍርት ..... 12
ክፍል ሁለት ..... 13
ግኝቶች ..... 13
ፖሊሲዎች ፤አዋጆች ፣ ደንቦች እና መመሪያዎች መዘጋጀታቸውን በተመለከተ ..... 13
ማእከሉ የበሽታ ፍንዳታ ሲከሰት ወቅታዊ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረቡን በተመለከተ..... 16
ማእከሉ ብቃት ያለው የላብራቶሪ አሰራር የዘረጋና ደረጃውን የጠበቀ ምርምራ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤ ..... 19
ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ..... 22
ማዕከሉ ወቅታዊ የበሽታዎች ምርመራ እና አሰሳ የሚያካሄድ መሆኑን በተመለከተ ..... 23
የምርመራ ቴክኒክ እና የሥራ ሂደት ብቃትን በይበልጥ በማጎልበት ዓለም አቀፍ ዕውቅና ማስገኘቱን በተመለከተ..... 25
ማእከሉ የሚያደርገው ጥናት የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት ..... 26

መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 26

ማዕከሉ የበሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት ........ 27

የሚሆኑ ጉዳዮችን የሚለይ መሆኑን በተመለከተ ........ 27

ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ ያለው እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 28

ማእከሉ የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት መሰራቱን በተመለከተ ........ 30

ማእከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት  መዘርጋቱና ተግባራዊ ........ 30

ማድረጉን በተመለከተ ........ 30

የምርመራ ማዕከሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ  ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማመንጨቱን በተመለከተ ........ 32

የምርመራ ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 33

ማዕከሉ የሀገሪቱን  የእንስሳት ጤና መረጃዎችን በመሰብሰብ ፤በማጠናቀር  እና በሰነድ መልክ የያዘ መሆኑን በተመለከተ ........ 34

ማእከሉ ሙያዊ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ ........ 36

የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም ስለመገንባቱ በተመለከተ ........ 37

ማዕከሉ የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱን በተመለከተ ........ 38

ማእከሉ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገናን የሚያካሂድ መሆኑን በተመለከተ ........ 40

ማዕከሉ የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን ማጎልበቱን በተመለከተ ........ 41

ክፍል ሶስት ........ 43

መደምደሚያ ሀሳቦች ........ 43

ክፍል አራት ........ 45

የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 45

አባሪ 1 ........ 48

መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ........ 48

## ድርሞ

## /Executive Summery/

ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥና የአቅም ግንባታ አፈጻጸምን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን መገምገም ተጠያቂነትንና ግልጸኝንነትን ማጠናከር እንዲሁም የአሰራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ ሲሆን ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**በኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች**

- ማዕከሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የእንስሳት ጤና በላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት መሠረት የእንስሳት ጤና ችግሮች መፍቻ መንገዶች (የፖሊሲ አቅጣቻጫ) ያለው መሆኑን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፣ በአገር ደረጃ የእንስሳት የጤና ፖሊሲ የሌሌ ሲሆን ማዕከሉም የመተዳደሪያ ደንብ ቢያዘጋጅም ጸድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጫማሪ የላቦራቶሪ አወጋገድ ፖሊሲ ወይም መመሪያ ባለመኖሩ በአገራችን በተለያየ አከባቢ የሚገኙ እንስሳቶች ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የተጋለጡ መሆናቸው የታወቀ መሆኑ እና በፖሊሲው መሰረት መመሪያ ያልወጣ መሆኑ፣ እንዲሁም ማዕከሉ ከሚያከናዉናቸዉ ተግባሮች አኳያ የፀደቀ የተቋቋመበት ደንብ ስለሌለዉ፣ ህጋዊ የስራ ድርሻዉን በግልፅ የሚያስቀምጥ ሰነድ አለመኖሩ፣ በመሆኑም በእንስሳት ጤና ላይ እንደ ሀገር ከፍተኛ ችግር እያመጣ ያለው ሲሆን እነኚም በእርድ ወቅት በሽተኛ እንስሳት እንዴት እንደሚወገድ የህግ ክፍተት (የአወጋገድ ህግ ያልተዘጋጀ) መሆኑ፣ ለህብረተሰቡ ከካሳ አከፋፈል አንስቶ የወጣ መመሪያ ወይም ድንብ ባለመኖሩ፣ የላቦራቶሪ ተቋማት ምርመራ በሚያካሂዱበት ወቅት ፖዘቲቭ የሆኑትን እንስሳት የሚያስወግዱበት መመሪያ ባለመኖሩ በሽታው እየተስፋፋ የሚሄድ መሆኑና ስጋውንና ወተቱን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጤና ላይ ችግር እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑ፤
- ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሄ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በወቅቱና በአፋጣኝ በመለየት ለተገልጋዮች በሚጠበቀው ደረጃ በተሟላና ብቃት ያለው መፍትሔ አለመስጠቱ ፤ የእንስሳት የጤና ችግር እንዲስፋፋ እና በእንስሳት ዘርፍ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖና ጉዳት እንዲደርስ አንዱ ምክኒያት ሊሆን የሚችል መሆኑ፣

- ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራን ውጤት ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ሊጠብቅ የሚያስችል ብቃት ያለው የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት በሚጠበቀው ደረጃ ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ፣ ላቦራቶሪው መርምሮ በላካቸው ላይ የኳራንቲን ክፍል ጨምሮ እንስሳትን በመላካቸው (አባ ኪያ ጄኔራል ትሬዲንግ ወይም በረከት ደመቀ)፣ ሳያስመረምሩ በመላካቸው (የሀጂ ሀሰን ዲዳ) እንዲሁም ከአገር ለሚወጡ እንስሳት፣ የላቦራቶሪውን ተዓማኒነት የሚያጎድፍ እና የበሽታዎች ምርመራ በሚጠበቀው ደረጃ እየተከናወነ ባለመሆኑ አሰራሩ ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ በማድረግ አገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ ትችል የነበረውን ጥቅም እንዳታገኝ እንዲሁም በግለሰቦችና በአገር ላይ የኢኮኖሚና የምስል (ሥም) ላይ ተፅጽኖ የሚያደርግ መሆኑ፣
- ማእከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ባለመስጠቱ በእንስሳት እርባታ ኑሮአቸው የተመሰረተው አርብቶ አደሮች የእንስሳዎቻቸውን ጤንነት በመጠበቅ በተሻለ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ መሆኑ፣
- ማዕከሉ በሚጠበቀው መጠን የበሽታ አሰሳዎችን (በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ በሶስት ዓመት አስራ ሁለት ጊዜ የበሽታ ጥናት ማድረግ ሲገባው ነገርግን ማእከሉ መስራት ከሚገባቸው በታች ያከናወኑ መሆኑ፣ እንዲሁም በሽታ ፍንዳታ ወይም ክስተት እንዲመረመርላቸው ከክልላዊ ላቦራቶሪዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች በከፊሉ መልስ አለመሰጠቱ፣ በሀገራችን የሌሉ ባእድ የሆኑ በሽታዎች ቢከሰቱ ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ፣ ድንበር አካባቢዎችን ግንዛቤ ለመፍጠር አውደ ጥናት ለማካሄድ ቢታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ፣ በአጠቃላይ ማእከሉ በኦፐሬሽናል ማኑዋሉ በተገለፀው መሰረት በመፈፀም በአገራችን ያለው የእንስሳት በሽታ አይነት፤ስርጭት፤እና ስፋትን በመገምገም ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግና ችግሩ ሲከሰትም አፋጣኝ መልስ ለመስጠት የሚያስችል ስራ በአግባብ አለመስራቱ
- ማዕከሉ ከዚህ በፊት በምርመራው ከሚታወቀው ሁለት የምርመራ ዓይነት ማለትም አቭያን እንፍሉዌንዛና ኒውካስትል እውቅና ያገኘ ሲሆን በሌላ የበሽታ ዓይነቶች እውቅና ለማግኘት እየሰራ መሆኑ፣
- ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን በተሟላ ሁኔታ የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት አለማድረጉ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲሰራጭ አለመደረጉ እንዲሁም ጥናቶቹ የህብረተሰቡን መሰረታዊ ችግሮች ላይ እንዳያተኩሩ እና ህብረተሰቡም የምርምር ውጤቶችን በአግባቡ ወደ ስራ አውሎ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረገ መሆኑ፣

- የምርመራ ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በህብረተሰቡ ጤና ላይ እና በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ተፅጽኖ የሚያሳድሩ በሽታዎችን በመለየት ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች በማቅረብ በዘርፉ የልማት አጀንዳዎች እንዲቀረጽ ግብዓት የሚሆን መረጃ ስለማመንጨቱ ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን በዘርፉ ለሚታዩ ችግሮች ቀጣይነት ያላቸው ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄዱ ባለማድረግ ዘርፉን በሳይንሳዊ ምርምር ታግዞ እዳያድግ አንዱ ምክንያት መሆኑ፣
- ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ እንዲኖር ያልሰራ እና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ፣ የስታንደርድ ኦፕሬሽን ሲስተሙ እንዳለ ሆኖ የናሙና አወጋገድ ሥርዓት ከሳይንስ ባለፈ ህጋዊ (በአገሪቱ ህግ) ሥር ሆኖ ባለመወጣቱ ወደ አገር የሚመጡት ናሙናዎች የሚያመጡት ተፅጽኖ ለማወቅ ድርሻውን ያልተወጣ መሆኑ፣
- ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ያመጡትን ተጸዕኖ በመለየት የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት አለመስራቱ እና እርምጃ አለመውሰዱ በላቦራቶሪ ናሙናዎች አማካኝነት በሚከሰቱ በሽታዎች በእንስሳት እና በሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ የሚችል መሆኑ፣
- ማዕከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት መዘረጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ የላቦራቶሪ ናሙና አቀባበሉ ከማዕከሉ ግቢ ውጭ ባለው ስርዓት በባለሙያ ናሙናው ተወስዶ ወደ ናሙና ቅበላ / ሳምፕል ረሰፕሽን/ ክፍል ያለው ሂደት በማንዋል በመሆኑ ጊዜ የሚፈጅና የተንዛዛ የመረጃ ልውውጥ መኖሩ፣ የላቦራቶሪ ናሙና አቀባበል ረጅም ጊዜ የሚወስድ እና በርካታ ተዋናዮችን የሚወስድ (ከገበሬ፣ የቀበሌ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የወረዳ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የዞን እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል ላቦራቶሪ እና መጨረሻ ላይ ማዕከሉ የሚደርስ በመሆኑ፣ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ በሚከሰት ወቅት በሽታ በብዛት እንዲሰራጭ በር የሚከፍት ሲሆን ከ2018 በፊት የነበረው መረጃዎቹ በኤሌክትሮኒክ ባለመሆኑ ፍጥነት የለሌ ሲሆን ሁሉም መረጃ ፈላጊ አካል መረጃውን በቀላሉ ለማግኘት የማይቻል፣እንዲሁም የበሽታ ቅኝት እና አሰሳ ሪፖርት ተቀናጅቶ በሰነድ መልክ የማይቀመጥና ለሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት በማሰራጨት ከመረጃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ እንዲሁም የመረጃ ሂደቱ ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ እንስሳቶቹ እንዲጎዱ የሚያደርግ መሆኑ፣

- ማዕከሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ስለማመንጨቱ የሚያሳይ ሰነድ ያልተገኘ ሲሆን የበሽታ መረጃ ተጠናቅሮ ተንትኖ አልተሰራጨም፡፡

- ማዕከሉ ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር በተለያዩ ማለትም በበሽታ ምርመራ ስልት ፣ መልካም ተሞክሮ መጋራት ፣ አብሮ የመስራት ባህል እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ የምርመራ ችግሮች ሁሉ ወደ ማዕከሉ በመምጣት ለሁሉም በተፈለገው ሁኔታ መልስ እንዳይሰጥ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፣

- በአገሪቱ ከ2008 ዓ.ም እስከ አሁን ያለው የበሽታ ዓይነት፣ የጉዳት መጠን፣ የሚገኙበት ቦታ፣ በዝርዝር ተተንትኖ ያለ ስለመሆኑ ለማጣራት ማስረጃ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም መረጃዎች ስለመኖራቸው ማስረጃ ወይም ሰነድ ያልቀረበ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በቦረና ዞን፣ በደቡብ ክልል፣ በሉሜ ወረዳ፣ በምስራቅ ሸዋ፣ እና በድሬ ደዋ እንስሳት ጤና ጽ/ቤቶች እንደ አገር የእንስሳት በሽታ መረጃ በማጣታቸው የበሽታ ቁጥጥር ለማድረግ የተቸገሩ መሆናቸው፣

- ማዕከሉ በወተት ልማት ፣ በኤክስፖርት ቄራዎች እና በደሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሙያዊ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአደአ ወተት ማቀነባበሪያ ድርጅት የህብረት ስራ ማህበር ከፍተኛ የእንስሳት ጤና ችግር ያለባቸው መሆኑ ፣ ይህም የማዳቀል ችግር ፣ ጥጆች በሚወለዱበት ጊዜ በብዛት የሚሞቱበት እና አካለ ስንኩላን የሆኑበት ሁኔታ መኖሩ፣ በብዛት የሚወለዱት ጥጆች ወንዶች መሆኑ ፣ይህ ደግሞ እንስሳቶችን ለማራባት አስቸጋሪ እየሆነባቸው መሆኑ እንዲሁም በላሞች ላይ የጡት መደፈን በሽታ የሚከሰትበት ሁኔታ መኖሩ ፣ እንዲሁም በአለማ ዶሮ ፈርሚስ ኃ.የግ.ማ የIB በሽታ ለመመርመር አቅም አለመፍጠሩ ፣ የደሮ በሽታ በትንፋሽ የሚተላለፈ ስለሆነ ብዙ ዶሮዎችን እየገደለ እና እንቁላል እልዳይጥሉ እያደረገ ከባድ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ መሆኑ፣

- የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን ክፍተት በመለየት የእያንዳንዱ የክልል ላቦራቶሪዎች በክፍተታቸው መሰረት እንዲሁም ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የስልጠና ዓይነቶችና የምርመራ ስልት ባለየ መልኩ የክልል ላቦራቶሪዎች አቅም በሚፈለገው አኳኃን ባለመገንባቱ እና እስፔሻላይዝ ባለመደረገቸው አንዱ በሌላ ላቦራቶሪ ዓይነት ሌላኛውን መርዳት ባለመቻሉ ሁሉም የክልል ላቦራቶሪዎች ለአንድ ዓይነት ምርመራ ማዕከሉን በማጣበብ የተሸለ ስራ እንዳይሰራ የሚያደርግ መሆኑ፣

- የክልል እንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎችም ስልጠና መውሰዳቸውን ያልደበቁ ሲሆን የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ግን ካላቸው ችግር እና ክፍተት አንጻር በቂ እንዳልሆነ ሲገልጹ በተጨማሪም የሚሰጣቸው ስልጠና ዝርዝር ወጥቶ ፣ ታቅዶበት እና ዒላማ ኖሮት የሚሰጣቸው ሳይሆን ከድርጅቶች ስፖንሰር ሲያገኙ የሚያሰለጥኑ መሆኑን እንዲሁም በማዕከሉ ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶች ላይ ለክልላዊ ላቦራቶሪዎች ምን ዓይነት ስልጠና መቼ እንደሚሰጥ ያልታቀደ መሆኑ ፣ ለክልሎች የሚሰጠው ሥልጠና የስልጠና ደሰሳ ጥናት ሳይደረግ ፣ የክልል ላቦራቶሪዎቹ ፍላጎትና ችግር ሳይታወቅ የሚሰጥ መሆኑ፣ እንዲሁም በክልል የአስተዳደር እርከኖች እስከ ወረዳ ባለው የእንስሳት ጤና ዘርፎች በአብዘኛው ሥልጠና ባያገኙም የሚያገኙት በአጋጣሚ ሲሆን ችግሩን መሰረት ያላደገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል
- ማዕከሉ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች በተወሰኑ የበሽታ ዓይነት እስፔሻላይዝ አድርገው እንዲሰሩ እውቅና ያልተጠ መሆኑና ክልላዊ የእንስሳት ላብራቶሪዎችን በማብቃትና በማወዳደር  ደረጃ የማይሰጥ በመሆኑ  አንድ ላበራቶሪ በአንድ የእንስሳት በሽታ ስፔሻላይዝ እንዲያደርግ የህብረተሰቡን የእንስሳት ጤና ችግር ትኩረት ሰጥቶ እንዳይፈታ ሊያደርግ የሚችሉ መሆኑ፣
- የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አስተዳደር እንደሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ያልገነባ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ማዕከሉ በሌላ አካል የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ለማስጠገን እና ለመለካት ወይም ካሊብሬት ለማድረግ ከ2008-2010 ዓ.ም አንድ መቶ ሰማኒያ አራት ሺህ አምስት መቶ ስድሳ ሁለት ብር ከሀያ ዘጠኝ ሳንቲም ወጪ እንዲያደርግ ያደረገ ሲሆን ሌሎች በክልል የሚገኙ ላቦራቶሪዎች መሳሪያዎች በጥገና ምክንያትና በባለሙያዎች አቅም ውስንነት ምክንያት የላብራቶሪ መሳሪያዎች ከስራ ውጭ የሆኑ መሆኑ፣
- ማዕከሉ የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን ማጎልበቱን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በታዩት በድሬደዋ እና አዳማ ኳራንቲኖች  እንዲሁም  በሉና እና አላና ሥጋ ኤክስፖርት ቄራዎች በስልጠናም ይሁን በሙያዊ ምክር  ምንም ዓይነት ዕገዛ ተደረጎላቸው የማያቅ መሆኑን፣
- የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም በመገንባትና በማስተባበር ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ፣ በበሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፣የምርመራ ማዕከሉ ለክልል ላቦራቶሪዎች የሥራ ላይ ሥልጠና የሚሰጥ ቢሆንም ነገር ግን ሥልጠናውን የሚሰጠው ታቅዶበት ሳይሆን እንደ አጋጣሚ መሆኑ፣

በማዕከሉ ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶች ላይ ለክልላዊ ላቦራቶሪዎች ምን ዓይነት ሥልጠና መቼ እንደሚሰጥ ያልታቀደ መሆኑ፣ ለክልሎች የሚሰጠው ሥልጠና የስልጠና ደሰሳ ጥናት ሳይደረግ፣ የክልል ላቦራቶሪዎቹ ፍላጎትና ችግር ሳይታወቅ የሚሰጥ መሆኑ፣ እንዲሁም በክልል የአስተዳደር እርከኖች እስከ ወረዳ ባለው የእንስሳት ጤና ዘርፎች በአብዘኛው ሥልጠና ባያገኙም የሚያገኙት በአጋጣሚ ሲሆን ችግሩን መሰረት ያላደገ መሆኑ፣

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. አገራችን ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ያላት ስትሆን 53.4 ሚሊዮን የቀንድ ከብት፣ 25 ሚሊዮን በጎች፣ 22.78 ሚሊዮን ፍየሎች እና 49.3 ሚሊዮን ዶሮዎች እንዲሁም 4.9 ሚሊዮን የባህላዊ፣ 41,687 የሽግግርና 144,258 የዘመናዊ ቀፎዎች እንዳላት በCSA (Central Statistics Authority), 2010/2011 እ.ኤ.አ መረጃ ያስረዳል፡፡
2. ከእንስሳት የሚገኘው ምርትና ምርታማነት ዝቅተኛ ከመሆኑ ምክንያት የሃገራችን የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ዝቅተኛ ነው፡፡ የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት፣ የውጪ ምንዛሬ በማስገኘትና የውጪ ምርቶችን በመተካት ረገድ ከፍተኛ ሀገራዊ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ከእንስሳት ሀብታችን ተገቢውን ጠቀሜታ ላለማግኘትና ምርትና ምርታማነትን በአግባቡ ማሳደግ እንዳይቻል እንቅፋት ከሆኑት ዋነኛ ምክንያት  በቂ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አለመሟላት ሲሆን፣ በ2013 እኤአ በCSA የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው 16.5 በመቶ የአገሪቱ GDP፣ እና 35.6% ከእርሻ የሚገኘው GDP ከእንስሳት የሚገኝ ቢሆንም ነገር ግን አገሪቱ በአማካይ በዓመት 150 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በእንስሳት በሽታ  በእንስሳት ሞትና፣ ምርት በመቀነስ ምክንያት አጥታለች፡፡
3. በመሆኑም የአገራችንን  እንስሳት ምርታማነትና የእንስሳት ውጤቶች ጥራት ለማሻሻል በዓለም ገበያ  ተቀባይነት ለማግኘት ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲቻል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ጠንካራና ደረጃቸውን የጠበቁ ተግባራት ማከናወን የሚችሉ ሆኖመገኘት ይኖርበታል፡፡
4. ከነዚህ ተግባራት ውስጥ ከዓለማቀፋዊ የንግድ ልውውጥ አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ድንበር ዘለልና ሌሎች ዋና ዋና በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ለመገምገም የሚያስችሉና አስተማማኝነት ያላቸው መረጃዎችን ከላቦራቶሪዎች በየጊዜው ማግኘት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
5. ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽዖዎች አማካኝነት በሽታዎች ገብተው ችግር እንዳይፈጥሩ ለመከላከልም ሆነ ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች አማካይነት በሽታ አምጪ ጀርሞች፣ ጎጂ ኬሚካሎችና የመድኃኒት ቅሬቶች እንዳይወጡ የሚደረጉ ምርመራዎችን በብቃትና ዓለም አቀፋዊ ተዓማኝነት ባለው ሁኔታ በማከናወን በገዥ አገሮች ዘንድ አመኔታን ለመፍጠር የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት የጎላ ድርሻ አለው፡፡

6. ለበሽታ መመርመሪያ፣ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሚያገለግሉ ኪቶችን (diagnostic kits) ክትባቶችን፣ መድኃኒቶችንና ሌሎች ባዮሎጅካሎችን የጥራትና ደህንነት ደረጃ በየጊዜው መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡በአገሪቱ እየተከናወኑ ያሉ የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር እርምጃዎችንም ሆነ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን አስተማማኝነት ያላቸውና የበሽታ ቁጥጥር አቅጣጫ ጠቋሚዎችና መሰረታዊ መረጃዎች አመንጪ እንዲሆኑ ለማስቻል በብቃት የተደራጀ ላቦራቶሪ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### የማዕከሉ አመሰራረት

7. ብሔራዊ የእንስሳት ምርመራና ጥናት ማዕከል በመጀመሪያ ሲቋቋም በማዕከል ሪፈራል የእንስሳት በሽታዎች ምርመራ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ማዕከላዊ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ላቦራቶሪ በሚል ሲያሜ ለሁለት ዓመት ሲሰራ ከቆየ በኋላ በግንቦት ወር 1989ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 79/89 አንቀጽ 17 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ተጠሪነቱ ወደ ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱት ተዛውሮ በዋናነት የምርምር ስራ እንዲያከናውን ታስቦ ብሔራዊ የእንስሳት ምርምር ማዕከል እየተባለ ሲጠራ ቆይቷል፡፡ ከመጋቢት 1999 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በማዕከላዊነት የሪፈራል ላቦራቶሪ መስጠት እንዲችል ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በሚል ስያሜ ተጠሪነቱም ለግብርና ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### የማዕከሉ ራዕይ

8. ተቀባይነት ያለው የእንስሳት በሽታ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤት እንዲመረት በማስቻል አገራችን ከእንስሳት ሀብቷ ተጠቃሚ ሆና ማየት ነው፡፡

### ተልዕኮ

- የእንስሳት በሽታዎችንና ጤና ችግሮችን መንስኤ መለየት፣
- በኢኮኖሚና በህብረተሰብ ጤና ላይ ከፍተኛ እንድምታ ባላቸው የእንስሳት በሽታዎች ላይ አሰሳና ቅኝት ማካሄድ፣
- ወደ ውጪ አገር ለሚላኩና ለሚገቡ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች የጤንነት ማረጋገጫ ምርመራ ማካሄድ፣
- የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን የበሽታ ምርመራ አቅም ማሳደግና የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስልቶችን መንደፍ እና ለተግባራዊነቱ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ናቸው፡፡

## የማዕከሉ የተሻሻሉ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት

9. በቀን 8/8/99 በደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 በወቅቱ ምክትል ጠቅላ ሚኒስቴር አቶ አዲሱ ለገሠ ማዕከሉ እንዲተገብር በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡
   1. የበሽታዎች ምርመራና አሰሳ ማካሄድ፣

- የእንስሳት በሽታ ፍንዳታና ወረርሽኝ ሲከሰትና ይህም ከክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ምርመራ ማከናወን፣
- ከፍተኛ ጉዳት በሚያርደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ አስተዋጽኦ ማድረግ፣
- ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኙ የእንስሳት በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን ውጤታማነት ለመከታተልና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የላቦራቶሪ ምርመራዎች ማካሄድ፣
- ከእንስሳት ወደ ሰው፣ ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎች ላይ የምርመራ፣ የቅኝትና አሰሳ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ጋር ማከናወን፣

2. ከአገር ለሚወጡና ወደ አገር ለሚገቡ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽዖዎች ምርመራ ማከናወን፣
    - ከአገር ለሚወጡ ወደ አገር ለሚገቡ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽዖዎች የበሽታዎች ምርመራ ማካሄድ፣
    - ለእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽዖዎች የመድኃኒት፣ ኬሚካል፣ ከባድ ብረቶችና ሆርሞኖች ቅሪት ወዘተ(drugs,chemicals, heavy metals, hormones, etc) ምርመራ በማድረግ በአገሪቱ የሚሰጠውን ዓለም አቀፍ የጤና ብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ማስቻል፣
3. የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም መገንባትና ማስተባበር፤
    - ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ፣ በበሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና መስጠት፣
    - በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ማድረግና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣
    - የላቦራቶሪ መገልገያና መጠቀሚያ መሳሪያዎች ኬሚካሎችና ባዮሎጅካልስ ግዥና አቅርቦት ችግር የሚሻሻልበትን ስልት መንደፍና በማስተባበር እገዛ ማድረግ፣
    - በከፍተኛ ወጪ በውጭ ምንዛሪ እየተገዙ የሚመጡ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም፣እንደዚሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም መገንባትና ለክልል ላቦራቶሪዎች ድጋፍ መስጠት፣
    - በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፣
    - በላቦራቶሪዎች ሥራ ለተሰማሩ የእንስሳት ጤና ምርመራ ባለሙያዎች ሊያገለግል የሚችል ወጥና ተመሳሳይ የሆነ አደረጃጀትና የደረጃ መስላል በማዘጋጀት የቴክኒክ ዕገዛ ማድረግ፣
4. በአገሪቱ ውስጥ በጥቅም ላይ እየዋሉ በሚገኙ የእንስሳት መድኃኒቶች ፣ ባዮሎጅካሎች፣ የምርመራ መገልገያ ቁሳቁስ (diagnostic- kits)ላይ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ውጤታማነታውን ማረጋገጥ፣
5. የማዕከሉን የምርመራ ቴክኒክና የሥራ ሂደት ብቃትን በይበልጥ በማጎልበት ዓለም አቀፋዊ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው ላቦራቶሪ እንዲሆን ማድረግ፣
6. የእንስሳት በሽታ ምርመራዎችንና መረጃዎችን በማደራጀትና በማቀናበር ማከማቸት፣ ለዓለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ አመቺነት ያለው በማድረግ

ከተመሳሳይ ተቋማት ጋር የባለ-ሙያ፣ የመረጃ፣የናሙና ልውውጥን በማዳበር የመርመራ አቅምን ማሳደግ፣

7. አገራዊ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ሥራዎችን ለመተግበር የሚያስችል የፕሮጀክት ሰነድ ማዘጋጀትና በማስተባበር የሚመለከታቸው ተባባሪዎች ሁሉ መተግበሩን መከታተል፣
8. የክልልና የፌደራል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች የሚካሄዱትን የእንስሳት ጤና ምርመራ ተግባራት ያለውን መሳሪያ ዓይነትና ብዛት፣ እንዲሁም የሰው ኃይል በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ መያዝ፣
9. የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ አጀንዳዎችን ለይቶ ማውጣትና ማቅረብ፣
10. የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችናመመሪያዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ እና ሲፀድቅም ሥራ ላይ ማዋል፣
11. የማዕከሉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የዕቅድ ክንውን ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
12. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

## የማዕከሉ ተገልጋዮች፣ ባለ ድርሻ አካላትና ተባባሪዎች

የእንስሳት ማዕከል ተገልጋዮች፣ ባለድርሻ አካላት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ተገልጋዮች

- አርሶ አደሩ፣ ከፊል አርሶ አርብቶ-አደሩና፣ አርብቶ አደሩ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎችና ማዕከላት፣
- የክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርናና እንስሳት ሀብት መ/ቤቶች፣
- በእንስሳት እርባታና ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለ-ሀብቶች፣
- መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች፣
- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣

## ባለ ድርሻ አካላት

- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎችና ማዕከላት፣
- የክልል እንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ላቦራቶሪዎች፣
- የተለያዩ የምርምር ተቋማት፣
- አለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት፣
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲሆኑ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

10. እንደሚታወቀው በአገራችን የሚገኙ አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና፣ አርብቶ አደሮች ኑሮአቸው የተመሠረተው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከእንስሳት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ደግሞ የእንስሳትን ጤና መጠበቅ አስፈላጊና ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡
11. በዚህም ረገድ የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል በአርሶ አደሮች በከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ይዞታ የሚገኙትን እንስሳት

ጤንነት ከመከታተል አንፃር በተለያ ወቅቶች ለሚከሰቱ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታዎች አስፈላጊውን ናሙና በመሰብሰብና የላቦራቶሪ ምርመራ በማድረግ ለበሽታ መከላከልና ቁጥጥር የሚረዱ መረጃዎችን ለሚመለከተው ክፍል በማቅረብ በሽታው የከፋ ችግር ሳያደርስ አስፈላጊውን የቁጥጥር ስራ በመስራት ጉልህ ድርሻው ማበርከት ይጠበቅበታል፣ በተጨማሪም በአገሪቱ የሚኖሩ አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና፣ አርብቶ አደሮች እንስሳት ላይ በተለያዩ ስነ ምህዳሮች ለኪሰቱ የሚችሉትን የእንስሳት በሽታዎች አሰሳና ቅኝት በመካሔድ የበሽታውን የስርጭት አድማስ ማወቅና አስፈላጊውን የቁጥጥር ስልት እንዲነደፍ መረጃ ማቅረብ እንዲሁም በአገር ውስጥ የሌሉና ነገር ግን ስጋት የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ የእንስሰት በሽታዎችን አሳሰና ቅኝት በማድረግ ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብና በመተንተን ለሚመለከታቸው ክፍሎች የማቅረብ ሀላፊነት ተጥሎበታል፡፡

12. በሚኒስቴሩ ከሚገኙ ከተለያዩ መምሪያዎችና ማዕከላት ጋር ያለውን የስራ ግንኑነት በተመለከተ

ማዕከሉ ከተሰጠው የስራ ሃለፊነት አንፃር ስራው የጋራ ትብብርና ቅንጅትን የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መምሪያዎችንና ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ማዕከላት ጋር ከእንስሳት ጤና ጋር የተያያዙ አስፈላጊ መረጃዎችን ከመለዋወጥ ጀምሮ በቅንጅት የሚሰሩ ስራዎችን አብሮ በማቀድና በመተግበር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ከእንሰሰት ዘርፉ የሚገኘወን ጥቅም ከፍ ለማድረግ ስራዎቸን ማከናወን ይጠበቅበታል ፡፡

13. ከክልል እና ዞን ወረዳ እንስሳት ሀብት መ/ቤቶች ጋር ያለውን ግንኙኙት በተመለከተ በአገሪቱ በሚገኙ ክልሎች ዞኖች እና ወረዳዎች የተለያዩ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ በሚከሰትበት ወቅት በተዋረድ በሚደረጉ ሪፖርቶች አማካኝነት ቦታው ድረስ በመንቀሳቀስ የበሽታወን መንስኤ በመለየት መረጃ የሚያቀርብ ሲሆን በተጨማሪም የክልል የእንስሳት ሀብት ቢሮዎች በሚያቀርቡት የባለሞያዎች ስልጠና ጥያቄ መሠረት ባለሞያዎችን ተቀብሎ በማሰልጠን ተገቢውን የአቅም ግንባታ ስራዎች ይሠራል፡፡

14. በእንስሳት እርባታና ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በተመለከተ የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል በተለያዩ የእንስሳት ዕርባታ ማለትም በወተት ላሞች በዶሮችና በሌሎች እንስሳት እርባታ ሥራ ላይ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ጋር የተለያዩ የእንስሳ በሽታዎች ምርመራና የምክር አግልግሎት በመስጠት ባለሀብቶች ጤናው የተጠበቀ የእንስሳት እና የእንስሳትና ተዋፅኦ ምርት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በማቅረብ ውጤታማ እንዲሆኑ የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በእንስሳት ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን የቁም እንስሳት ወደ ውጪ አገር ለመላክ በሚፈለጉበት ጊዜ እንደተቀባይ ሀገራት የበሽታ

ምርመራ ጥያቄ መሠረት ምርመራውን በማካሄድ አገሪቱ ከዚህ ዘርፍ የውጪ ምንዛሬ እንድታገኝ የበኩሉን አስቷዋፅኦ ያደርጋል፡፡

15. ከመንግሥታዊ የልማት ድርጅቶ ጋር በተያያዘ የልማት ድርጅቶች ከብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል ለማግኘት የሚፈልጉትን ድጋፍና ትብብር አስመልክቶ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መመርያንና ደንብን በጠበቀ መልኩና የማዕከሉ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን ትብበርና ድጋፍ ያደርጋል፡፤

16. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ያለውን የሥራ ግንኑነት በተመለከተ በአሁኑ ወቅት ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአገራችን ላይ እንሚገኙ ይታወቃል ከነዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በርካታ የሆኑ የእንስሳት ጤና ባለሞያዎችን በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በመጀመሪያ ዲግሪ፡ በማስተርስና በፒኤችዲ ዲግሪ በማሰልጠን ላይ የሚገኙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተማሪዎቹ ለምረቃ የሚያስፈልጋቸወን የምርምር ስራዎቻቸውን ለማከናወን እንዲችሉ ማዕከሉ በየዓመቱ በርካታ ተማሪዎችን በመቀበልና አሰፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ስራዎችን በመሥራት ላይ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪም ከተለያዩ ዩኒቨስሲቲዎች ጋር ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና በእንስሳት ጤና ጉዳት በሚያስከትሉ በሽታዎች ላይ የምርምር ሥራዎችንን በጋራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

17. የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ጋር ማዕከሉ የሥራ ግንኙነት ያለው ሲሆን ከክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች አቅም በላይ የሆነ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ በሚከሰትበት ጊዜ ከክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች በሚደርሰው ሪፖርት መሠረት አስፋለጊውን ናሙና በመሰብሰብ ውጤቱን የማሳወቅ እንዲሁም የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ራሳቸው የሰበሰቡትን ናሙና ወደ ማዕከሉ በሚልኩበት ጊዜ ተገቢውን የምርመራ አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪም የከክል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች የምርመራ አቅም ከመገንባት አንፃር ስልጠና በመስጠት የምርመራ ግብዓቶችንና የመመርመሪያ መሠሪያዎችን ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

18. ከተለያዩ የምርመር ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት በተመለከተ የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል በእንስሳት ምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያስከትሉ እንስሳት በሽታዎች ላይ ምርምር ከሚያከሂዱ ተቋማት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ያለውን አቅም በመጠቀመ የምርምር ስራዎች ይሰራል፡፡

19. ከአለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ጋር ያለው ግነኙነት በተመለከተ ምንም እንኳን ማዕከሉ ቀጥተኛ የሆነ ግንኑነት ባይኖረውም ማዕከሉ አለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያወጣቸውን የበሽታ ምርመራ ስታንዳርዶችን በመጠቀመና በየወቅቱ የበሽታ ፍንዳተ ሪፖርቶችን በሚመለከተው አካል

አማካኝነት እንዲደርስ ፣ አለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ባዘጋጀው ስታንዳርድ Perfoemance of Veterinary service(PVS) መሠረት አገሪቱ የምትገኝበትን የእንስሳት በሽታ የመመርምር አቅም በመገምገም በየወቅቱ ማሳወቅ አለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት በሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ወቅታዊ መረጃዎችን በማግኘት የተቀላጠፈና ወቅቱ የሚጠይቀውን የምርመራ አይነት ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡

20. መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶችን በተመለከተ የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል ከበርካታ መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶችጋር የስራ ግንኙነት ያለው ሲሆን ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር የተለያዩ ትብብሮችንና ድጋፎች በማግኘት የተሰጠውን ሀላፊነት ለመወጣት ጥረት ማድረግ፡፡

## የማዕከሉ አደረጃጀት እና የሰው ሀይል

21. ማዕከሉ ተጠሪነቱ ለግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ቁጥጥርና ክትትል ዳይሬክቶሬት ሲሆን በዋና ዳይረክተር የሚመራና በማዕከሉ ዳይሬክተር ሥር በአምስት የሥራ ሂደቶች የተዋቀረ ሲሆን፣ እነሱም፡- የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት፣ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣ የሰው ሀብት ልማትና ጠቅላላ አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚንኬሽን እና የኦዲት ጽ/ቤት ሲሆኑ በተጫማሪም የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር አስተዳደርና የባዮ ሴፍቲና ባዮ ሴኩሪቲ ክፍሎች ናቸው፡

## የሰው ኃይል

22. ማዕከሉ በመዋቅሩ መሰረት 303 የሰው ኃይል እንዲኖረው የተፈቀደለት ሲሆን በሥራ ላይ የለው የሰራተኛ ብዛት በ2008 ዓ.ም 176፣ በ2009 ዓ.ም 181 እና በ2010 ዓ.ም 212 ነው፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የተፈቀደ የሰው ኃይል ብዛት በቁጥር | | | በሥራ መደቡ ላይ ያለው የሰው ኃይል ብዛት | | | | | | | | | የተፈቀደው የሰው ኃይል በሥራ ላይ ካላው ጋር በመቶኛ ሲነጻጸር (%) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በ2008 ዓ.ም | በ2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | በ2008 ዓ.ም | | | በ2009 ዓ.ም | | | 2010 ዓ.ም | | | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| | | | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | | | |
| 303 | 303 | 303 | 58 | 118 | 176 | 59 | 122 | 181 | 68 | 144 | 212 | 57 | 59 | 69 |

**የፋይናንስ ምንጭ፡-**

23. ብሔራዊ የእንስሳት በሽታ ምርመራና ጥናት ማዕከል የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚመደብ ሲሆን በ2008፣ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመታት ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት እና ውስጥ ገቢ በጀት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት የተመደበ በጀት በብር | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| | 28,101,888.71 | 28,802,993.27 | 37,064,380 | 20,783,781.76 | 21,360,617.80 | 16,022,930.94 | 73% | 74% | 43% |
| | የካፒታል የተመደበ በጀት | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
| | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| | 24,607,652.50 | 11,315,156.23 | 9,500,000 | 22,968,491.33 | 7,833,790.22 | 2,689,284.75 | 93% | 69% | 28% |
| ድምር | 52,709,541.21 | 40,118,149.5 | 46,564,380 | 43,752,273.09 | 29,194,408.02 | 18,712,215.69 | 83% | 71.5 % | 35.5 % |

## የማዕከሉ አሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description) ፡-

24. የስራ ሂደቱ አሰራር ስርአት (Work flow) በተመለከተ ከላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ማዕከሉ የተለያዩ ስራዎችን ማለትም የበሽታ ምርመራ ፤ የአሰሳና ቅኝት እንዲሁም የምርምር ሥራዎችን አቅዶ የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ስራዎች ለመተግበር የአሰራር ስርአቱን ISO 17025 በሚያዘው መሠረት የዘረጋ በመሆኑ ከናሙና ቅበላ እስከ ውጤት መስጠት ድረስ ያሉ ሂደቶችን በሙሉ በተዘጋጁት ስታንዳርድ ኦፕሬቲንግ ፕሮሲጀሮችን (SOP) መሰረት የሚተገበሩ ናቸው፡፡

25. በዚህም መሠረት ለበሽታ ምርመራ፤ የአሰሳና ቅኝት እንዲሁም ለምርምር ሥራዎች የሚሆኑ ናሙናዎች ወደ ማእከሉ በሚመጡበት ጊዜ የናሙና ቅበላ ክፍል ባለው ስታንዳርድ ኦፕሬቲንግ ፕሮሲጀሮችን (SOP) መሠረት ናሙናዎችን ከተቀበለ በኋላ የናሙናዎችን የጥራት ደረጃ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት መምጣቱን ያረጋግጣል፡፡ ናሙናው በትክክለኛ ሁኔታ የመጣ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለናሙና መቀበያ በተዘጋጀው ፎርም መሠረት በመመዝገብና የላቦራቶሪ ኮድ በመስጠት የምርመራ ጥያቄ ወደ ቀረበለት ላቦራቶሪ ናሙናውን ይልከዋል፡፡

26. ናሙናው የተላከለት ላቦራቶሪ በተዘጋጀው ስታንዳርድ የምርመራ ዘዴ መሠረት ምርመራውን አከናውኖ ውጤቱን በተዘጋጀው ፎርም በመመዝገብ መልሶ ወደ ናሙና ቅበላ ክፍል ይልከዋል፡፡ የናሙና ቅበላ ክፍሉም የቀረበው የምርመራ ውጤት በሚመለከታቸው ክፍሎች መፈረሙን ካረጋገጠ በኋላ ደንበኞች መጀመርያ ናሙናውን ሲሞሉ ውጤቱ እንዴት እንዲላክላቸው እንደሚፈልጉ በጠቀሱት ዘዴ መሠረት የምርመራው ውጤት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

27. ማእከሉ ሌሎች የትብብር ሥራዎችንና ስልጠናዎች ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ ጥያቄው በማዕከሉ የበላይ ሀላፊዎች ከታመነበትና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ስራዎቹ እንዲሠሩ ለሚመከለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ በማድረግ ስራዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

| ተ.ቁ | አሰራር | የሥራ ሂደት |
|---|---|---|
| 1. | ናሙና እና መረጃ በማን ይሰበሰባል ? | በማዕከሉ ባለሙያዎች ናሙናው ከተሰበሰበ በኋላ የሚፈለገውን መረጃ አሟልተው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለላቦራቶሪው ያስረክባሉ፣ |
| | | በክልል ላቦራቶሪ ባለሙያዎች፣ |
| 2. | ናሙና እና መረጃ ለላቦራቶሪው እንዴት ይገባል? | በናሙናና መረጃ መቀበያ ዩኒት በናሙናና መረጃ ተቀባይ ሰራተኛ ይሰራል፣ |
| | | ናሙናና መረጃ ተቀባይ ሰራተኛ የላቦራቶሪውን መለያ ቁጥር ይሰጣል፣ |
| | | መረጃው በመረጃ ቋት ይመዘገባል፣ |
| | | የናሙናና መረጃ ተቀባይ ሰራተኞች ለሚመለከተው ላቦራቶሪ ናሙናና መረጃ ያስተላልፋሉ፣ |
| 3. | የበሽታ ፍንዳታ ሪፖርት አደራረግ | የበሽታ ፍንዳታ በክልሎች በሚኖርበት ጊዜ መረጃው የሚደርሰው በአብዛኛው በእንስሳት ጤና ቁጥጥር መምሪያ በኩል እንዲሁም ከክልል ላቦራቶሪዎች የመመርመር አቅም በላይ ሲሆን በቀጥታ ከነዚሁ ላቦራቶሪዎች ሪፖርት ይደረጋል፡፡በዚህም ጊዜ ማዕከሉ በሽታውን ለማጣራት ባለሙያዎችን ይመድባል፣ ባለሙያዎችም ቦታው ድረስ በመሄድ አስፈላጊውን ናሙናና መረጃ እንዲሰበስቡ ይደረጋል፡፡ |
| 4. | ናሙና ተመርምሮ ለደንበኛ ሪፖርት የሚደረግበት ጊዜ አማካይ | 10 ቀናት |
| 5. | የምርመራ ውጤት በማን ይጠናቀራል? | የበሽታ ፍንዳታ ምርመራ ከሆነ በመስክ የበሽታውን መንስኤ ለማጣራት የሚሄደውን ቡድን የሚያስተባብረው ሀኪም፣ |
| | | ለውጪ ገበያ ለሚቀርቡ የእንስሳት የጤና ማረጋገጫ ምርመራ ከሚያካሄዱ ሀኪሞች አንዱ፣ |
| | | አሰሳና ቅኝት ከሆነ ኢፒዲሞሎጅስቱ፣ |
| 6. | የተጠናቀረው የምርመራ ውጤት እንዴት ለደንበኛ ይደርሳል? | በማዕከሉ ኃላፊ ፊርማ ሪፖርቱ በመዝገብ ቤት በኩል ደንበኛው በአካል በመምጣት፣ በፋክስ፣ በኢሜይል፣ ወይም በፖስታ፣ አስፈላጊ ሲሆን በቀጥታ ስልክ፣ |
| 7. | የአገልግሎት ክፍያ | የለም |
| 8. | የአድቮኬሲ ሥራዎች፣ | በማዕከሉ ደረጃ በራሪ ፅሁፎች፣ ፖስተሮች ማዘጋጀት |
| 9. | የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና ክትትል፣ | የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ክትትል አናሳ ሲሆን ጥገና ሲያስፈልግ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ወይም በሌሎች ድርጅቶች እንዲጠገኑ ይደረጋል፣ለወደፊት ግን መለስተኛ የጥገና ዎርክሾፕ እንዲቋቋም ታሳቢ ተደርጓል፡፡ |
| 11. | የላቦራቶሪ መረጃ አያያዝ በተመለከተ፣ | የላቦራቶሪ አያያዝ ስርዓት /laboratory information management system/ተግባራዊ አልሆነም፣ ያለው አሰራር ደካማ በመሆኑ የኋላ ታሪክ መረጃዎችን / traceable informations/ ለማግኘት አይቻልም፣ |

## የኦዲቱ ዓላማ፡-

28.የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በማዕከሉ ሁለገብ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ፣ የእንስሳት በሽታ አሰሳና ቅኝት፣ የእንስሳት በሽታ ጥናት፣ በማዕከሉ የሚሰጡ የአቅም ግንባታና ምክር አገልግሎት ሥራዎች፣ እንዲሁም የማዕከሉ የመረጃ ሥርዓትና ከባለድርሻ አካላት እና ተገልጋዮች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ የማዕከሉ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በመገምገም በአሰራር ላይ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ችግሮቹን ለማሻሻል እና ለመቀነስ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

## የኦዲቱ ወሰን

29.የደሰሳ ኦዲቱ የተከናወነው በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ሲሆን ኦዲቱ የሚሸፈነው ከ2008-2010 ዓ.ም የተከናወኑ የማዕከሉ ክንውኖች ላይ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

30.በኦዲቱ ወቅት ከማእከሉ አሰራር ጋር የተያያዙ ሰነዶችን በመከለስ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከማእከሉን የስራ ሃላፊወች እና ባለሙያወች ጋር ቃለመጠይቅ በማድረግ፤በናሙና ተመርጠው ከታዩ ለወላይታ ሶዶ ላቦራቶሪ፣ ለወላይታ ሶዶ ዞን፣ እንስሳትና አሳ ሀብት ጽ/ቤት፣ ለያቤሎ ላቦራቶሪ፣ ለቦረና ዞን አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የእንስሳት ጤና ዳይሬክቶሬት፣ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ ለሉሜ ወረዳ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ ለአዳማ ኳራንታይን ኃላፊዎች፣ ለስሪቃ በዳሶ የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት፣ ለአባ ኪያ ጀነራል ትሬዲንግ፣ ለሂርና ክልላዊ እንስሳት ጤና ላቦራቶሪ፣ ለጅግጅጋ እንስሳት ጤና ላቦራቶሪ፣ ለድሬ ደዋ እንስሳት ጤና ላቦራቶሪና ለድሬ ደዋ ኳራንታይን ቃለ-መጠይቆች በማድረግ በአካል ተገኝቶ አሰራሩን በመገምገም መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኑል፤፤

## የኦዲት አከባቢ

31.የኦዲቱ አካባቢ የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማእከል ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም ኢኮኖሚያወዊ፤ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤የሚል ሲሆን ለዚህ የኦዲት አካባቢ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫወች እና ሁለት ንኡስ የኦዲትየትኩረት አቅጣጫወች ተለይተዋል፡፡

## የኦዲትየትኩረት አቅጣጫወች እና የኦዲት መመዘኛ መስፍርት

### የኦዲትየትኩረት አቅጣጫወች

1. ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ማዕከል የሚያከናውናቸው የእንስሳት ጤና ምርመራ፣ የእንስሳት በሽታ አሰሳና ቅኝት እንዲሁም የጥናት ሥራዎች ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም፣
    1.1. ማዕከሉ የሚያከናውናቸው የእንስሳት ጤና ምርመራ፣ የበሽታ አሰሳና ቅኝት ሥራ ብቃት እና ውጤታማነትን መገምገም፡፡
    1.2. ማዕከሉ የሚያከናውናቸው የጥናት ሥራዎች ውጤታማነትን መገምገም፣
2. የምርመራ ማዕከሉ ውጤታማ የባዮ ሴኪዩሪቲና ባዮ ሴፍቲ ሥርዓት መዘርጋቱንና የአፈጻጸሙን ውጤታማነት መገምገም፤
3. የምርመራ ማዕከሉ ድጋፍ አሰጣጥ ፣ የመረጃ ሥርዓትና ሥርጭት ውጤታማነትን መገምገም፣የሚሉ ናቸው፤፤

### የኦዲት መመዘኛ መስፍርት

4. ለዝርዝር ኦዲቱ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን (Evaluative Criteria) ለማዘጋጀት የሚከተሉት መረጃዎች መሰረት ተደርገዋል፡፡ በአባሪ ተያይዟል

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### ፖሊሲዎች ፣አዋጆች ፣ ደንቦች እና መመሪያዎች መዘጋጀታቸውን በተመለከተ

32. ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲ ፣ አዋጅ ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሊያቀርብ እና ሲፀድቀም ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

33. ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን ፣ አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ሲፀድቁም ሥራ ላይ እንደያውል በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በተጻፈ በደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 ገጽ 4 ተግባር እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

34. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪን በሚመለከት የእንስሳት ጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲ እና መመሪያዎችን እንዳላዘጋጀ ታውቋል፤፤እንዲሁም ማእከሉ የተቋሙን ረቂቅ የማቋቋያ ደንብ ያላዘጋጀ ቢሆንም ረቂቅ ደንቡ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

35. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የማዕከሉን ረቂቅ ማቋቋሚያ ደንብ በኢንስቲትዩት ደረጃ በማውጣት የበለጠ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ሰነዱ ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተተችቶ በግብርና ሚኒስቴር ህግ ክፍል የታየ ሲሆን ነገር ግን በሚኒስትሩ ፊርማ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ያልተላከ እና ውሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ይህንኑ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

36. የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለማእከሉ በቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የማእከሉ ማቋቋሚያ ደንብ ተዘጋጅቶ እና በተደጋጋሚ ታርሞ ለዋናው መሥሪያ ቤት በ2006 ዓ.ም ገቢ ያደረጉ ቢሆንም እስካሁን መልስ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ሆኖም የማዕከሉ የመፈጸምና የማስፈጸም መብት ህጋዊ ድጋፍ ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ማዕከሉ በዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ስታንዳርድን (OIE- Standards) ለምርምር ፣ ለአሰሳ እና ቅኝት ስራዎች ተግባራዊ በማድረግ ለሕብረተሰብ ጤና ችግር የሆኑ በሽታዎች ላይ እየሰራ መሆኑን እንዲሁም ይህንን አሠራር ሀገራዊ ለማድረግና ብሔራዊ

የላቦራቶሪ አሠራር ስታንዳርዶችን አውጥቶ ለማላመድና ለመተግበር የሚያስችለው ሕጋዊ ሰነድ (የሕግ ድጋፍ) ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

37. በሌላ መልኩ የማእከሉ የበላይ ሃላፊዎች ማእከሉ ለምን የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲና አስፈላጊ መመሪያወችን አዘጋጅተው እንዲጸድቅ ያላቀረቡት ለኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችንና መመሪያዎችን የሚያወጣ የግብር ሚኒስቴር ሥልጣን መሆኑን የገለጹል ሲሆን፤፤ከግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ በቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ በግብርና የገጠር ልማት ፖሊሲ ውስጥ ማካተታቸውንና ለብቻ ለእንስሳት ጤና ፖሊሲና መመሪያ ያልወጣ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. በተጫማሪም የማዕከሉ ኃላፊ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪዎችን የሚያዘጋጀው የግብርና ሚኒስቴር መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች አዘጋጅቶ ለማፅደቅ ማእከሉ እራሱ በቅድሚያ በአዋጅ የጸደቀ ኃላፊነት ሊኖረው ስለሚገባ በማዕከሉ የተዘጋጀው ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ኢንስቲትዩትን ማቋቋሚያ ረቂቅ ሰነድ ሊጸድቅ ይገባል ብለዋል፡፡

39. ሆኖም ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ ማዕከሉ በእንስሳት ጤና ዙሪያ ፖሊሲዎችን፣ እና መመሪያዎችን በማውጣት የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር እገዛ ያላደረጉ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል የሆነው ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን ፣ አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ሲፀድቁም ሥራ ላይ እንዲያውሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በተጻፈ በደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 ገጽ 4 ተግባር እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

40. በሌላ በኩል የFMD (Foot and mouth disease) በሽታ በሀገራችን ሥርጭቱ ከ40-70 % በደም ናሙና ቅራሪና በቫይረስ ልየታ ምርመራ በአገራችን መኖሩ ማዕከሉ ያረጋገጠው ሲሆን ነገር ግን በሽታው ሊስፋፋ የቻለበት ምክንያት የቁጥጥር ስትራቴጂ በአገር አቀፍ ደረጃ ቢዘጋጅም ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ ምክንያት መሆኑን ገልጸው የበሽታ ስርጭትን የጉዳት መጠን የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያለው የበሽታ መቆጣጠርያና መከላከያ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ማዕከሉ ብዙ የመረጃ ምንጭ ቢሆንም ይህንን አቀናብሮ ለመምራት የዕውቀት ፣ የልምድ፣ የበጀትና ግልፅ የሆኑ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች በተሟላ መልኩ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ባለመኖራቸው ብዛት ያላቸው የእንስሳት ጤና ችግሮችን ለመቅረፍ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ማዕከሉ በሽታው የተስፋፋበት የቁጥጥር ስትራቴጂ

በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው ባለመተግበሩ ነው ቢሉም፣ ከባለ ድርሻ አካላቱ ማእከሉ አንዱ ሲሆን የተሰጠውን ሥራ ድርሻ በአግባቡ አልተወጣም፡፡

41. ማዕከሉ የፀደቀ መቋቋሚያ ደንብ የሌለው እና ህጋዊ የስራ ድርሻዉን በግልፅ የሚያስቀምጥ ሰነድ አለመኖሩ፣ እንዲሁም ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ያላቀረበ መሆኑ እንዲሁም የማዕከሉ ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ቢዘጋጅም ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ በአገር ደረጃ ብዙ የእንስሳት ጤና ችግሮች እያጋጠሙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዋናዋና ችግሮችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ (በላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት መሠረት የእንስሳት ጤና ችግሮች መፍቻ መንገዶች (የፖሊሲ አቅጣቻጫ) ባለመኖራቸው በአየር ላይ የሚንሳፈፉ ቫይረሶች እንዲስፋፉና በኤፍ ኤም ዲ የመሳሰሉ በሽታወች የአገራችንን የቤት እንስሳትን በስፋት የሚጠቁበትን እድል እንዲሰፉ አድርጓል፤ የማዕከሉ የሥራ ሃላፊዎች በምክንያት ጥያቄ እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ መሰረት እንስሳቶች በአብዛኛው በኤፍ ኤሚ ዲ የተያዙ መሆኑ እንዲሁም የእንስሳት ጤና ፖሊሲ ባለመኖሩ የእንስሳት ጤና አጠባበቅን በተመለከተ ከየት ተነስቶ የት መድረስ እንደሚገባ የሚያመላክትና አቅጣጫን የሚጠቁም ሰነድ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡
- እንዲሁም በእንስሳት ጤና ላይ እንደ ሀገር ከፍተኛ ችግር እያመጡ ካሉት ውሰጥ በእርድ ወቅት በሽተኛ እንስሳት እንዴት እንደሚወገዱ ወይም የአወጋገድ ህግ ያልተዘጋጀ መሆኑ ፣
- የላቦራቶሪ ተቋማት ምርመራ በሚያካሄዱበት ወቅት ፖዘቲቭ የሆኑ እንስሳትን የሚወገዱበት መመሪያ ባለመኖሩና የማይወገዱ በመሆኑ፣ በሽተኛ የሆኑ እንስሳት በሽታቸው ወደሌሎች እንስሳት እንዲስፋፋ ከማድረጉም በተጨማሪ የእነዚህን እንስሳት ስጋቸውን እና ወተታቸውን የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የጤና ችግር እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በድሬ ደዋ እና በጅግጅጋ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ከእንሳሳት ወደ ሰው እና ከሰው ወደ እንስሳት እንዲሁም ከእንስሳት ወደ እንሳስት የሚተላለፉ በሽታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ የሚገዙ

  እና የሚሸጡ ህብረተሰቦችን ማስቆም የሚያስችል ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ችግር እያመጣ መሆኑን፣ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፤፤
- እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ቃለ መጠይቅ ካቀረበላቸው እና ከሰነድ ክለሳ በተገኙ ማስረጃዎች የያቤሎ ክልላዊ የእንስሳት ላቦራቶሪ ፣ የአዳማ

ኳራንታይን ጣቢያ ፣ የድሬ ደዋ ኳራንታይን ጣቢያ ከሌላ ሀገር የሚመጡ ድንበር ዘለል እንስሳዎች በሽታዎችን ይዘው ወደ ሀገር እንዳይገቡ ለመከላከል የሚያስችል ፖሊሲም ሆነ መመሪያ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በድንበር አካባቢ ያሉ እንስሳቶች ከጎረቤት ሀገሮች እንስሳት ጋር አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ በመኖሩ የድንበር ዘለል በሽታ ሊመጣ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም ነገርግን ችግሩን ለመከላከል በሀገር ደረጃ የሪፍት ቫሊ ፊቨር በሽታ ምርመራ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. በአጠቃላይ ማእከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት የማዕከሉን የማቋቋሚያ ደንብ ረቂቅ አዘጋጅቶ እንዳቀረበ ሁሉ የእንስሳት ጤናን በሚመለከት ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ሲፀድቁም ሥራ ላይ እንዲውል ባለማድረጉ እና ያዘጋጀው ረቂቅ ደንብም ያልጸደቀና ስራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች በአገሪቱ የሚከሰቱና ከሌሎች አካባቢ የሚመጡ በሽታዎችን በአግባቡ ለመከላከልና የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ካለማስቻሉም በላይ አገሪቱ ከዘርፉ በወጪንግድ ተወዳዳሪ እና ተጠቃሚ እንዳትሆን በከፊል ምክንያት ሆኗል፡፡

## ማእከሉ የበሽታ ፍንዳታ ሲከሰት ወቅታዊ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረቡን በተመለከተ

43. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሂ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በመለየት ለተገልጋዮች በወቅቱ የመፍትሔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

44. በማዕከሉ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በሐምሌ 2001 የተዘጋጀ ገጽ 11 ላይ በበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሔ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ክስተቶች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በማረጋገጥ ለተገልጋይ በወቅቱ የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ይገልጻል፡፡

45. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች፤ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል ላቦራቶሪዎች እና ባለድርሻ አካላት የስራ ሃላፊዎች፤ጋር በተደረጉ ቃለመጠይቆች እና የዶክሜንት ክለሳዎች መሰረት ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሂ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በመለየት ለተገልጋዮች በወቅቱና አፋጣኝ የመፍትሔ ሃሳብ ከማቅረብ አንፃር ጉልህ ክፍተትና ውስንነት እንደነበረበት በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ጉዳዩን አስመልቶ በኦዲት ቡድኑ የተሰበሰቡት ማስረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በድሬደዋ እና በጅግጅጋ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች፣ ማእከሉ የሚሰበሰባቸው ናሙናዎች ውጤት ቶሎ የማይመለስ ወይም ማዕከሉ ያስቀመጠው አማካይ

የናሙና መመለሻ ጊዜ 10 ቀናት ቢሆንም፣ ከ21 ቀናት በላይ የሚቆይ መሆኑን ፣ናሙናው የሚጠፋበት ሁኔታ መኖሩ እና ውጤቱ የማይመለስበት አጋጣሚ መኖሩን፣ በዚህም ምክንያት የበሽታውን መንስኤ የማይታወቅበት ሁኔታ በመኖሩ ብዙ እንስሳት ህክምና አጥተው የሚሞቱበት ሁኔታ እና ከፍተኛ ኢኮኖሚዊ ጉዳት የሚከሰትባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለመጠይቅ እና የሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በአላጌ ቴክኒክ ኮሌጅ በበሽታ ፍንዳታ ምክንያት 65 እንስሳት መሞታቸውን፣ ከሰኔ 2015 እስከ መጋቢት 2018 ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን አርሲ ነገሌ በበሽታ ፍንዳታ ምክንያት 50 አህያዎች መሞታቸውን፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ሉሜ ወረዳ የእንስሳት ጤና መምሪያ ከእንሳሳት ወደ ሰው እና ከሰው ወደ እንስሳት እንዲሁም ከእንስሳት ወደ እንሳስት የሚተላለፉ በሽታዎች ላይ እሰካሁን ድረስ የተሰራ ስራ አለመኖሩን ፣የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፤፤
- የአለማ ፋርሚስ ድርጅት IB (infectious bronchitis) የሚባል የዶሮ በሽታ ናሙና እንዲመረመርለት ያቀረበ ቢሆንም መመርመር ባለመቻላቸው ብዙ ዶሮዎችን እየገደለ እና እንቁላል እንዳይጥሉ እያደረገ ከባድ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን በ2008 51,335፣ በ2009 52,549፣ በ2010 133,518 በድምሩ 237,402 ዶሮዎች ተመርምረው እርምጃ እንዲወሰድ ባለመደረጉ ከአንድ ድርጅት ብቻ (አለማ ዶሮ ፋርምስ) መሞታቸው እንዲሁም ድርጅቱ ጫጩቶቹን አስፈልፍሎ ለገበሬዎች እና ለሌሎች ድርጅቶች የሚያሰራጭ በመሆኑ እና በሽታውም በትንፋሽ የሚተላለፍ በመሆኑ የተሰራጩት ዶሮዎች ከበሽታው ጋር የሚሰራጩበት ሁኔታ በመፈጠሩ በሽታው ወደ ሌሎች ዶሮዎችም ሊተላለፍ የሚችል መሆኑን፣ የድርጅቱ የስራ ሃላፊ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፤፤
- በያቤሎ፣ በሂርና፣ በጅግጅጋና በድሬደዋ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች የበሽታ ምርመራዎቹ ከአቅማቸው በላይ በሚሆንበት ጊዜ ናሙናውን ወደ ብሄራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ እና ጥናት ማእከል የሚልኩ መሆኑን ነገር ግን ቶሎ ምላሽ ከመስጠት አንፃር ችግር ያለ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከገበሬዎች ጋር ግጭት የሚፈጥርባቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱት ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ማዕከሉ በነባራዊ ሁኔታ በሰጠው መልስ ባለፉት 3 (ሶስት) ዓመታት በውጪ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት የተወሰነ የውጪ ምንዛሪ ቢፈቀድም ግዢው በመራዘሙ ምክንያት የተሟሉ የመመርመሪያ Reagents (ሪኤጀንቶች), Diagnostic Kits (የመመርመሪያ ኪቶች)፣ የላቦራቶሪ መገልገያ ዕቃዎች (Lab Consumables) ባለመኖራቸው ምክንያት

ደንበኞችን በሚፈለገው ጥራትና የጊዜ ገደብ መልስ በመስጠት ማርካት ያልተቻለበት ሁኔታ የነበረ መሆኑን ነገር ግን ማዕከሉ በራሱ ጥረት የተጠቀሱትን ማቴሪያሎች ከውጪ Development Partner (የልማት አጋሮች) በተለያዩ ዘዴዎች በመጠየቅና በማስገዛት የበሽታ ፍንዳታዎች፣ የአሰሳና ቅኝት፣ የቁም እንስሳት ምርመራ ሥራዎችን በማከናወን ለብዙዎቹ እፎይታ/ መልስ ለመስጠት የተቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47. ከዚህ በተጨማሪ ማእከሉ ከተሰጠው ተልኮ አንጻር ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ እየሰጠ እንደሚገኝ ለተገልጋዮች የተላኩትን ግብረመልሶች በመመልከት መረዳት እንደሚቻል ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ በግብዓት እጥረት ወይም ከዚህ በፊት በሽታው በሀገር ውስጥ ሪፖርት ያልተደረገ ከሆነ ናሙናውን ወደ ውጭ በመላክ እንዲሰራ የሚያደርጉ  መሆኑን ሆኖም ውጤቱ ሊዘገይ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

48. በአለማ ፋርሚስ ድርጅት IB (infectious bronchitis) በሚባል የዶሮ በሽታ ተከሰተ የሚባለው የሞት መጠን በጣም የተጋነነ እና ከቫይረሱ ባህሪ አንጻር ይህን ያህል ሞት የማያደርስ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፋርሙ የቀረበው ቅሬታ ምንም መሰረት የሌለው መሆኑን በፋርሙ በመገኘት ማረጋገጥ ችለናል፣ እንዲሁም በሀገሪቷ ውስጥ ያሉትን ወረዳዎች በሙሉ ለማዳረስ የማይቻል መሆኑን ነገር ግን ሳይንሳዊ በሆነ የናሙና አወሳሰድ መስፈርት መሠረት የተወሰኑ  ወረዳዎችን በማካተት ሀገሪቷ በተለያዩ በሽታዎች ያለበትን  ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችሉ ሥራዎች የተሰሩ መሆኑን በምሳሌነት በAvian Influenza, RVF ECF, Bovine TB etc - High risk area፣) ገልጸዋል፡፡

49. ይሁንና በአለማ ፋርሚስ ድርጅት  የሞቱትን ዶሮዎች የሚያሳይ ሰነድ በውጭ አገር ናሙና ተልኮ የተመረመረ የምርመራ ውጤት ማስረጃ፣ እና ድርጅቱ ለኦዲት ቡድኑ የሰጠው ቃለ መጠይቅ ያለ በመሆኑ፣ በቦታው ተገኝተን ችግሩ አለመኖሩን ማረጋገጥ ችለናል የተባለው በምን ሊረጋገጥ እንደቻለ  የሚያሳይ ሰነድ ከነባራዊ መልሱ ጋር ያልቀረበ በመሆኑ፣  የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

50. በተጨማሪም ማእከሉ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ የIB በሽታው ያንያህል ሞት አያደርስም ለተባለው ጉዳይ ማስረጃውን ከአለማ ፋርሚስ ድርጅት የቀረበ ሲሆን፣ በተጨማሪም ማእከሉ ባስጠናው እና ባቀረበውን አባሪ 13 ላይ ከተመረመሩት 134 ዶሮዎች 115ቱ 85% የ IB በሽተኞች መሆኑን  እየታወቀ አይገልም ማለቱ አግባብነት የለውም፡፡

51. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሄ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች  ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በወቅቱና በአፋጣኝ በመለየት ለተገልጋዮች በሚጠበቀው ደረጃ የተሟላ መፍትሔ አለመስጠቱ የእንስሳት የጤና ችግር እንዲስፋፋ

እና በእንስሳት ዘርፍ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖና ጉዳት እንዲደርስ አንዱ ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡

**ማእከሉ ብቃት ያለው የላብራቶሪ አሰራር የዘረጋና ደረጃውን የጠበቀ ምርምራ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤**

52. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራን ውጤት ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ሊጠብቅ የሚያስችል ብቃት ያለው የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ከአገር ለሚወጡና ወደ አገር ለሚገቡ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽዖዎች ውጤታማ እና ተዓማኒነት ያለው የበሽታዎች ምርመራ ሊያደርግ ይገባል፡፡
53. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች፤ ከኳራንቲኖች፤ እንዲሁም ከቁም እንስሳት ላኪ ድርጅቶች የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት የማእከሉ የላብራቶሪ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጡ ለውስጣዊና (ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ናሙና እንዲሰበስብ ጫና የሚያሳድር መሆኑ) እና ውጫዊ ተፅጽኖዎች የተጋለጠ እና የላብርቶሪ ምርመራ ውጤቱም የተቀባይነት ችግሮች እንደነበሩበት በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች በተደጋጋሚ እንደተከሰቱ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፤፤
54. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ ማዕከሉ ከአለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የእንስሳት ጤና ሪፈረንስ ላቦራቶሪዎች የብቃት ንጽጽር ምርመራ በማድረግ 100% የውጤት ስምምነት ማግኘቱን ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ለማስረጃ በአባሪ 14ና15 ያቀረቡት በሞለክዩላር እና በሴሮሎጅካል ምርመራዎች ጥራት ያለው ሥራ የተሰራ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ሰነዶችና ከቀረቡት ቃለመጠይቆች የማዕከሉን የምርመራ ውጤት መሰረት አድርገን የጤና ሰርትፍኬት ሰጥተናል ብለው ተልከው ችግር ያለባቸው እንስሳት እና ድርጅቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
    - ወደ ውጭ የሚላኩ የቁም እንስሳት ከመጀመሪያው በኳራንታይኑ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የምርመራ ናሙናዎች ተቀድቶ ማዕከሉ ሊደርስ ሲገባው ነገር ግን የማዕከሉ ባለ ሙያዎች ቀጥታ የላቦራቶሪ ናሙናዎችን የባለ ሀብቶቹ እንስሳት ማቆያ ቦታ ሂደው ቀድቶ የሚያመጡ ሲሆን፣ ይሄም ከባለ ሀብቶች ጋር የጥቅም ንክኪ ሊፈጥ የሚችል መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ከማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎችና ከኳራንታይኖች እንዲሁም ከቁም እንስሳት ላኪ ድርጅቶች ከተደረገ ቃለመጠይቅ ታውቋል፡፡
    - ስሪቃ በዳሶ የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት ማዕከሉ በቀን 24/02/2016 በSR/Ex58/16 በ test report No, 58/16 የመረመረውን በአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ በቀን 22/06/2008 ዓ.ም በማዕከሉ የጤና ምርመራ

ተደርጎላቸው ወደ ዱባይ የተላኩ ሲሆን ዋጋቸው 110,000 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ እንስሳቶች በሻርጃ /ዱባይ ጤንነታቸው የተሟላ አይደለም ተብለው በቦታው እንዲቃጠሉ የተደረገ መሆኑ፣

- አባ ኪያ ጄነራል ትሬዲንግ (በረከት ደመቀ) የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት በአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ በቀን 09-11/06/2016 በ SR/Ex267/16 test report No, 58/16 በtest report No, 267/16 በማዕከሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው 900 ፍየሎችን ወደ ዱባይ ሻርጃ የተላኩ ቢሆንም ከ900 ፍየሎች 61 ፍየሎች ብቻ ተቀባይነት ሲያገኙ ቀሪወቹ ማለትም 59,780 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ ፍየሎች ተቀባይነት ባለማግኘታቸውወደ ሀገር የተመለሱና ለአውሮፕላን መጓጓዣ 46,970 የአሜሪካ ዶላር ኪሳራ እንዳጋጠመ ለማወቅ መቻሉ፤፤
- ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪ ማዕከሉ በቀን 25-27/06/2017 በ SR/Ex259/17 በtest report No, 259/17 በማዕከሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪ ለ2500 ፍየሎች ለ21 ቀናት በኳራንታይን ጣቢያ ውስጥ እንዲቆዩና ለአባ ሰንጋ፣ የበጎች ደስታ መሰል በሽታ፣ ፈንጣጣ እና የፍየል ሳንባ በሽታ ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት የወሰዱ መሆኑን ጠቅሶ እ.አ.አ በቀን 21/04/2017 በእንስሳት ጤና ሰርትፍኬት ቁጥር AQS-01/397/2017 ከአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ የተሰጣቸው ቢሆንም፣ ከ2500 ፍየሎች ውስጥ 1298 ወይም ዋጋቸው 90,860 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ በተለያየ ቦታ የሞቱ መሆኑና በጅቡቲ የወደብ አገልግሎት ዋጋ ብር 4,322,222.7 ላኪው እዲከፍሉ መጠየቁ ታውቋል፤፤

55. ጉዳዩን አስመልክቶ የማእከሉ የበላይ ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የማዕከሉ ሠራተኞች ናሙና እንዲሰበስቡ የተደረገው በሁኔታዎች አስገዳጅነት ማዕከሉ ተገፍቶ የገባበት እንጂ ችግሩን ሳያውቀው ቀርቶ እንዳልሆነ ገልፀው ይህን ጉዳይ በተመለከተም ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴርና ለኳራንቲን ክፍል ደጋግመው ያሳሰቡና (በደብዳቤ ቁጥር በ85/165/11/1510/09) እንዲሁም (በደብዳቤ ቁጥር በ85/165/11/238/09) የጠየቁ ቢሆንም ለጊዜው ኳራንቲን ክፍሉ ናሙናውን ለመሰብሰብ ዝግጁ ባለመሆኑ ሥራው አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲቀጥል መደረጉን ገልፀዋል፤፤

56. እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር የስሪቃ በዳሶ የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅትን አስመልክቶ ለቀረበው ግኝት በሰጡት መልስ በ24/02/2016 ምርመራ የተደረገላቸው የናሙና ቁጥራቸው ከ2772-3838 የሆኑ 1067 በጎች 26/02/2016 በSR/Ex58/16 በ test report No, 58/16 ውጤቱ በሽታው የተገኘባቸው

እንስሳት እንዳይላኩ በማስገንዘብ በአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ ሠራተኛ በሆኑት በአቶ አብይ ጫላ በኩል የተላከ እንጂ ለቁም እንስሳት አቅራቢዎች ያልተሰጠ ሲሆን ማዕከሉ የምርመራ ውጤቱን ለቁም እንስሳት አቅራቢዎች የማይሰጥ በመሆኑ መረጃው ከየት ተገኝቶ እንደቀረበ ግልፅ አይደለም በማለት የገለጹ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ ማስረጃውን ያገኘው ከአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ በመሆኑ፣በማእከሉ ሃላፊዎች የተሰጠው መልስ በዚህ መሰረት ሊቃኝ ይገባዋል፡፡

57. ከዚህ በተጨማሪ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር የአባ ኪያ ጄነራል ትሬዲንግ (በረከት ደመቀ) የቁም እንስሳት ላኪን በተመለከተ ለቀረበው ገኝት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫቸው በሰጡት መልስ ሀምሌ 12/2008 ዓ.ም ዱባይ ከሚገኘው ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ቆንስላ ጄኔራል ፅ/ቤት በቁጥር ETHCON 3-/019/16 ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ መነሻነት Rukn Al Barka Livestock trading በሚባል ኢትዮጵያዊ አስመጪ ድርጅት ወደ ዱባይ ከላካቸው 854 ፍየሎች መካከል FMD, Rift Valley Fever እና Brucellosis በሽታ ተገኝቶባችዋል በሚል ወደ አገር እንዲመለሱ ወይንም እንዲቃጠሉ በዱባይ የአየር ለውጥና አካባቢ ሚኒስቴር ትዕዛዝ መሰጡቱን አስመልክቶ የእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኔስቴር ማዕከሉን በዚህ ጉዳይ ሃሳብ እንዲሰጥ በጠየቀው መሰረት ማዕከሉ በደብዳቤ መልስ የሰጠበት ቢሆንም (በደብዳቤ ቁጥር በ85/165/11/51/08) በተመሳሳይ ሁኔታዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተደረገው የማጣራት ሥራ ለምርመራ ያልቀረበ እንስሳት ጭምር እንደተመረመሩ ተደርጎ የተላኩ እንስሳት መኖራቸውን ለማወቅ የተቻለበት ሁኔታ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

58. እንዲሁም የማእከሉ የበላይ ሃላፊዎች ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪን በተመለከተ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበው ግኝት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በ28/06/2017 ናሙናውን የተቀበሉ መሆኑን 05/07/2017 የምርመራ ውጤት ሪፖርቱን ዝግጁ ቢደረግም የሚመለከታቸው ክፍሎች ውጤቱን መጥተው መውሰድ በሚገባቸው ጊዜ ባለመውሰዳቸውና በመዘግየቱ ለተፈጠረ ችግር ማዕከሉን ተጠያቂ መሆን እንደማይገባ ገልጸዋል፡፡

59. በተጨማሪም የማእከሉ ኃላፊው በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ የሀጂ ሀሰን ድዳ ፍየሎቹ ከውጭ ከተመለሱ ከሁለት ወር በኋላ በ28/06/2017 የ897 ፍየሎች ናሙና ተሰብስቦ በመመርመር በ04/07/2017 ውጤቱን ያዘጋጁ ሲሆን ነገር ግን ፣ የአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ በቀን 21/04/2017 የእንስሳት ጤና ሰርትፍኬት ቁጥር AQS-01/397/2017 ለ2500 ፍየሎች የጤና ሰርትፍኬት የሰጣቸው ሲሆን፣ የአዳማ ኳራንቲን ማዕከሉ መርምረው ውጤት ከመስጠቱ ከሁለት ወር በፊት ማለትም በቀን21/04/2017 የጤና ሰርትፍኬት የሰጠ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ የተቀበለ ሲሆን ችግሩ የተፈጠረው የአዳማ ኳራንቲን ከማዕከሉ ወይም ከሌላ አካል የጤና ምርመራውን ሳይቀበል በመላኩ ነው፡፡ በመሆኑም ፍየሎቹ የሞቱበት ምክንያት ከእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር ባለሙያዎች ባቀረቡት ሪፖርት ፍየሎቹ በPPRV መጠቃታቸውን ከተከለሱት ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. በመሆኑም ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራን ውጤት ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ሊጠብቅ የሚያስችል ብቃት ያለው የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት በሚጠበቀው ደረጃ ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ፣ ላቦራቶሪው መርምሮ በላካቸው ላይ የኳራንቲን ክፍል ጨምሮ እንስሳትን በመላካቸው (አባ ኪያ ጄኔራል ትሬዲንግ ወይም በረከት ደመቀ)፣ ሳያስመረምሩ በመላካቸው (የሀጂ ሀሰን ዲዳ) እንዲሁም ከአገር ለሚወጡ እንስሳት፣ የላቦራቶሪውን ተዓማኒነት የሚያጎድፍ የበሽታዎች ምርመራ በሚጠበቀው ደረጃ እየተከናወነ ባለመሆኑ አሰራሩ ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ በማድረግ አገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ ትችል የነበረውን ጥቅም እንዳታገኝ እንዲሁም በግለሰቦችና በአገር ላይ የኢኮኖሚና የምስል (ሥም) ላይ ተፅጽኖ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ

61. ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
62. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከማዕከሉ የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ከቦረና አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ ከያቤሎ ክልላዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእንስሳት ጤና ቁጥጥር ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ከድሬ ደዋ እና ከጅግጅጋ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክሜንት ክለሳወች መሰረት ማዕከሉ በአከባበው ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት እንደማይሰጥ ለማወቅ ተችሏል፤፤
63. ስለ ጉዳዩ የማእከሉ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአርብቶ አደሮች አከባቢ የተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ሰጥተው እንደማያቁ ገልጸው ይሄንን ሥራ የሚሰራው የክልል የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች መሆናቸውን አስረድተዋል፤ የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ባካሄዳቸው የመስክ ግምገማዎች የክልል የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች በአርብቶ አደሮች አከባቢ የተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት እንደማይሰጡ የታወቀ በመሆኑና በማዕከሉ 2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ገጽ 5፣ ላይ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ የነበረ በመሆኑ በማዕከሉ ሃላፊዎች የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፤፤
64. በሌላ መልኩ የኦዲት ቡድኑ አዘጋጅቶ ለማእከሉ ባቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የማዕከሉ የበላይ ሃላፊወች በሰጡት መልስ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ጤና ጥበቃና የላቦራቶሪ አገለግሎት፤ መስጠት ቢቻል እጅግ አስፈላጊ ስራ መሆኑን ሆኖም ይህንን አገለግሎት ለመስጠት በቂ ባለሙያ፣ ተሽከርካሪ ፣ግብዓት ፣ሎጀስቲክ እና የቅንጅት ሥራ የሚፈልግ መሆኑን እንዲሁም ማዕከሉ ይሄንን ሥራ

ለመስራት በ2011 ዓ.ም ዕቅድ አለመያዙን ነገርግን ቢተገበር ለአርብቶ አደሩ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ ይታመናል ብለዋል፡፡

65. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት የማዕከሉ ሃላፊ በሰጡት መልስ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ወካይ የሆኑ እንስሳት ላቦራቶሪዎች ይገኛሉ፣ በመሆኑም እነዚሁ ላቦራቶሪዎች ሥራቸውን በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰሩ የአቅም ግንባታዎች ተሰርቷል ብለዋል፡፡ ነገር ግን ማእከሉ ያቀደውን ሥራ ሁሉ እንዲፈጽም የኦዲት ቡድኑ ያምናል፡፡

66. በመሆኑም ማእከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ባለመስጠቱ በእንስሳት እርባታ ኑሮአቸው የተመሰረተው አርብቶ አደሮች የእንስሳዎቻቸውን ጤንነት በመጠበቅ በተሻለ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል ፡፡

## ማዕከሉ ወቅታዊ የበሽታዎች ምርመራ እና አሰሳ የሚያካሄድ መሆኑን በተመለከተ

67. ማዕከሉ በኦፕሬሽናል ማኑዋሉ መሰረት በዓመት አራት ጊዜ የበሽታዎች አሰሳና ምርመራ በማድረግ ወቅታዊ የበሽታ ጥናት ማድረግ ይጠበቅበታል፤፤

68. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች፤በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በቦረና፣ በደቡብ ክልላዊ መንግስት፣ በሉሜ ወረዳ፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን፣ በጅግጅጋ፣ በድሬደዋ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክሜንት ክለሳዎች መሰረት ማእከሉ በኦፕሬሽናል ማኑዋሉ በተገለፀው መሰረት በአመት አራት ጊዜ የበሽታዎች አሰሳና ምርመራ በማድረግ ወቅታዊ የበሽታ ጥናት የማያካሂድ መሆኑ፣

69. የማዕከሉ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ማዕከሉ የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት እና የምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት (RVF,ECF) በሽታዎች በዓመት አራት ጊዜ ጥናት ሰርተን ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት አቀርበናል ቢሉም ስለመስራቱ የሚሳይ የስራ ዕቅዶች ፣ እና የክንውን ሪፖርቶችን ቢያቀርቡም በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑና የአፈጻጸም ሪፖርት ተብለው የቀረበው ሪፖርት የማእከሉ ስለመሆኑ የሚገልጽ የመዝገብ ፕሮቶኮል ያልተሟላ በመሆኑ የኦዲት ቡዲኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

70. በሌላ መልኩ ስለጉዳዩ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ለነባራዊው ሁኔታ መግላጫ በሰጡት መልስ አሰሳ እና ቅኝት ስራዎች በአመት 4 ጊዜ መሰራት አለበት የሚል እቅድ ያልተቀመጠ ቢሆንም በዝርዝሩ የተጠቀሱት ቦታዎች አሰሳ እና ቅኝት እንዲሰራባቸው የተመረጡ ቦታዎች አለመሆናቸውን ለአሰሳ እና ቅኝት የተመረጡት ቦታዎች በጋምቤላ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በቦረና እና በሱማሊ ክልል ለ RVF እና ለ ECF ፣ በሀይቅ እና ረግረጋማ ቦታዎች (በቢሸፍቱ፣ ዝዋይ፣ ባህርዳር እና አርባምንጭ) ለ AI መሆኑን አሰሳ እና ቅኝቱ የሚሰራውም የግድ በዓመት 4 ጊዜ ሳይሆን ያሉት የበሽታዎች ስጋት እየታየ 2 ግዜ

በዓመት ወይም እንደ አስፈላግነቱ ከ4 ጊዜ በላይም ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ገልጻዋል፣

71. የማእከሉ ዋና ዳይሬክተር ይህን ይበሉ እንጂ ነገር ግን በማእከሉ ኦፕሬሽናል ማንዋል ገጽ 6፣ የፕሮጀክት ዶክመንት ላይ በተቀመጠው መሠረት ማዕከሉ በዓመት አራት ጊዜ፣ የበሽታ አሰሳና ቅኝት ዶክመንት እንደሚያዘጋጅና ሁለት ተላላፊ በሽታዎች፣ ሁለት የውስጥ ወይም የውጭ በሽታዎች ዶክመንት ተዘጋጅተው እንደሚሰሩ የሚገልጽ በመሆኑ፣እና የኦፕሬሽናል ማንዋል ላይ የሚገለፅ ነገር ተቋሙ እንዲተገብረው እንጂ ሲፈለግ የሚሰራበት ሳይፈለግ የሚተው ከሆነ የተሰጠው አስተያየት የኦፕሬሽናል ማንዋሉን ማዘጋጀት አስፈላጊ እንዳልነበርና ለተቋሙ ጥቅም የማይሰጥ ዶክሜንት እንደሆነ ስለሚያመላክት እንዲሁም ለቅኝትና ደሰሳ የተለዩ ቦታዎች ናቸው ተብለው በዋና ዳይሬክተሩ የተገለፁት በማዕከሉ ከዚህ በፊት እነዚህ ቦታዎች በጥናት ስለመለየታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣ በመስሪያቤቱ የበላይ ሃላፊ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡዱኑ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

72. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ ኃላፊ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ ሥራዎቹ ስለ መሰራታቸው በአባሪ 03፣04፣ 06፣07፣እና 08፣ ማስረጃ ነው ብሎ ያቀረቡትን የኦዲት ቡዱኑ ሲከልስ አባሪ 03 ስለ STDS reports for FMD, CBPP,PPR surveillance report ሲሆን ነገር ግን ሪፖርት ስለመሆኑና የመስሪያቤቱ ሰነድ ስለመሆኑ የሚያሳዩ ስራ ፕሮቶኮል፣ ማለትም የመ/ቤቱን ማህተም፣ የመዝገብ ቁጥር፣ የማዕከሉ ኃላፊ ሥምና ፊርማ የሌለው በመሆኑ የኦዲት ቡዱኑ እንደ ማስረጃ ለመቀበል ይቸገራል፡፡ በተጫማሪም በአባሪ 07 (surveillance strategic plan and ECF surveillance report) ላይ የቀረበው ዕቅድ፣እና የአፈጻጸም ሪፖርቱ የቀረበው ከእቅዱ በፊት በመሆኑ ማለትም ስትራቴጅክ እቅዱ በ2017 ሆኖ እያለ የአፈጻጸም ሪፖርት ተብሎ የቀረበው ማስረጃ የ2014፣2015 እና 2016 በመሆኑ ተዓማኒነት ይጎለዋል፡፡

73. በመሆኑም ማዕከሉ በሚጠበቀው መጠን የበሽታ አሰሳዎችን (በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ በሶስት ዓመት አስራ ሁለት ጊዜ የበሽታ ጥናት ማድረግ ሲገባው ነገርግን በኦፕሬሽናል ማኑዋላቸው መሰረት በሚጠበቀው ደረጃ ያልሰሩ መሆኑ፣

74. እንዲሁም በሽታ ፍንዳታ ወይም ክስተት እንዲመረመርላቸው ከክልላዊ ላቦራቶሪዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች በከፊሉ መልስ አለመሰጠቱ፣ በሀገራችን የሌሉ ባእድ የሆኑ በሽታዎች ቢከሰቱ ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ድንበር አካባቢዎችን ግንዛቤ ለመፍጠር አውደ ጥናት ለማካሄድ ቢታቀድም ያልተከናወነ በመሆኑ፣በአጠቃላይ ማእከሉ በኦፕሬሽናል ማናዋሉ በተገለፀው መሰረት በመፈፀም በአገራችን ያለው የእንስሳት በሽታ አይነት፣ስርጭት፣እና ስፋትን በመገምገም ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግና ችግሩ ሲከሰትም

አፋጣኝ መልስ ለመስጠት የሚያስችል ስራ አለመስራቱ በአገሪቱ የእንስሳት ሀብት ላይ የከፋ ችግር እዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፤፤

## የምርመራ ቴክኒክ እና የሥራ ሂደት ብቃትን በይበልጥ በማጎልበት ዓለም አቀፍ ዕውቅና ማስገኘቱን በተመለከተ

75. ማዕከሉ የማዕከሉን የምርመራ ቴክኒክና የሥራ ሂደት ብቃትን በይበልጥ በማጎልበት ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እና ተቀባይነት ያለው ላቦራቶሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ-መጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ማዕከሉ የምርመራ ቴክኒክ የሥራ ሂደት ብቃትን ለማጎልበት በአገር ውስጥ እና በውጭ አገሮች የባለ ሙያ ሥልጠና እንዲሁም የተለያዩ የምርመራ መሳሪያዎች ከተለያዩ አገራት በመጻጻፍ እርዳታ የሚያገኝ ሲሆን በውስን በሽታዎች ማለትም አቭያን እንፍሉዌንዛ እና ኒውካስትል ዓለም ዓቀፍ እውቅና እና የላቀ ብቃት ቢኖረውም በአንዳንድ በሽታዎችን የመመርመር አቅም ያልገነባ መሆኑታውቋል፤፤ እንዲሁም በውስን በሽታዎች ላይ ያሉትን ተቀባይነት ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን ወደ ሌሎች የበሽታ ዓይነቶች ዕውቅና ለማግኘት ሙከራ ቢያደርጉም እስከ አሁን በሂደት ላይ ያለ መሆኑ፣ የምርመራ አቅም ካልገነቡት የምርመራ ዓይነቶች ውስጥ ለዓብነት በአለማ ዶሮ ፋርምስ የIB (infectious bronchitis) በሽታ በተደጋጋሚ የይመረመርልን ጥያቄ ከተገልጋዮች ሲቀርብ የመመርመር አቅም ባለመፈጠሩ አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፤በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፤፤

77. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ማዕከሉ ለባለሙያዎቹ በየጊዜው ስልጠና የሚሰጥና ከአገራችን ሌላ የ13 የምስራቅ እና መካከለኛ አፍሪካ ላቦራቶሪዎች ደጋፊ ላቦራቶሪ መሆኑን እንዲሁም የዶሮ ፈንግል እና በርድ ፍሉ የሚባሉ ሁለት በሽታዎች ደግሞ በምስራቅ አፍሪካ ሪፈራል ላቦራቶሪ ከመሆኑ በተጨማሪ ደረጃውን የጠበቀ የላቦራቶሪ ኳሊቲ መናጅመንት ሲስተም ያለውና ISO1725 ከደቡብ አፍሪካ SANAS የሚባል አክሪዲቴሽን አካል አለም ዓቀፍ ዕውቅና እንዳለው ገልጸዋል፡፡

78. እንዲሁም የማእከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የመመርመር አቅም አለመፈጠሩ ሳይሆን የመመርመሪያ ኪቱ በውጪ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ተገዝቶ አለመቅረቡን በምክንያትነት ገልጸዋል፡፡

79. በተጨማሪም የማዕከሉ ሃላፊው በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ በአቭያን ፍሉ እና በኒውካስትል በሽታ ምርመራ ብቻ እውቅና እንዳለው ተደርጎ የተወሰደው ግንዛቤን በተመለከተ እውቅና ሰጪው አካል South African National Accreditation System (SANAS) የመጀመሪያውን የአምስት አመት ዕቅድና ዙር በግንቦት 2017 ኦዲት ባደረጉት ወቅት የሚጨርስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአቭያን ፍሉ እና ኒውካስትል በሽታ የሞለክዩላር

ምርመራ የኳሊቲ ማኔጅመንት ሲስተሙ በተደረገ ኦዲት በISO 17025፣ 2005 መሰረት የሚያስፈልገውን መመዘኛ ያሟሉ መሆናቸውን ተረጋግጦ እውቅናው እንዲቀጥል ሲፈቅድ ሌሎች 10 ሴሮሎጂ ቴስቶች ለሚያዚያ 2017 እንደገና እንዲታዩ ተወስኖ ነበር፣ በሌላ በኩል ማእከሉ አገር ውስጥ ካለው እውቅና ሰጪው አካል ማለትም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት በኩል እውቅናውን ማስቀጠል የተሻለ ሆኖ አግኝቷል ቢልም በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርመራው ኦዲት ተደርጎ እውቅና እንደሚቀጥልና ሌሎችን እውቅናዎችን የማግኘት እቅድ እንጂና ሥራዎቹ በሂደት ያሉ ከመሆኑ ውጭ እስከ አሁን ሌላ የተገኘ እውቅና በሂደት ላይ ያለ መሆኑ፣

80. በመሆኑም ማዕከሉ ከዚህ በፊት በምርመራው ከሚታወቀው ሁለት የምርመራ ዓይነት ማለትም አቭያን እንፍሉዌኔዛና ኒውካስትል እውቅና ያገኘ ሲሆን በሌላ የበሽታ ዓይነቶች እውቅና ለማግኘት፣ የማዕከሉ የምርመራ ብቃት ወደ ተለያዩ የምርመራ ዘዴዎች ባለማሳደጉ ሌላ ዕውቅና ማስመዝገብ የሚሞክረው እስከ አሁን አልተሳካም፡፡

## ማእከሉ የሚያደርገው ጥናት የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

81. የምርመራ ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት ሊያደርግ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተተርጉሞ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

82. ይሁን እንጂ ማዕከሉ ጥናት ሲያደርግ የነበረው የእንስሳት በሽታ ጥናት የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተቶርጉሞ መሰራጨቱን የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

83. በተጨማሪም ማዕከሉ አገራዊ የዳልጋ ከብቶች ነቀርሳ ላይ አዋጭ የቁጥጥር ስልት እንዲመረጥ ለማድረግ ጥናትና ምርምር እያደረገ መሆኑን ቢገልጽም በደቡብ ክልል እንስሳት ጤና ፣ ወላይታ ሶዶ ክልላዊ ላቦራቶሪ፣ ያቤሎ ክልላዊ ላቦራቶሪና በቦረና ዞን አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ ሉሜ ወረዳ እንስሳት ጤና፣ ምስራቅ ሸዋ እንስሳት ጤና፣ ሂርና ክልላዊ ላቦራቶሪ፣ ድሬ ደዋ ክልላዊ ላቦራቶሪ እንስሳት ጤና እንዲሁም ጅግጅጋ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች ማዕከሉ ምንም ዓይነት የእንስሳት በሽታ ምርምር ስለመስራቱ የማያውቁና ለትብብር ያልተጠየቁ መሆኑን እና የማእከሉን ጥናት እና ምርምር ያልተጠቀሙ መሆናቸውን የተለያዩ ሰነዶችን በመከለስ እና ለስራ ኃላፊዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን እንዲሁም የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን የሚከናወኑ የምርምር ውጤቶች ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተቶርጉሞ የተሰራጨበት

ሁኔታ የሌለ እና ለህብረተሰቡ የበሽታውን አደገኛነት ለማሳወቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተሰሩ ጥናቶች ለሚመለከታቸው አካላት ያልተሰራጩ መሆኑን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎችም አለመተጎርማቸውን እንዲሁም የክልሎችንና ባለ ድርሻ አካላት ፍላጎት ደሰሳ ጥናት አለመሰራቱን ገልጸዋል፡፡

85. ማእከሉ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ መልስ ብሎ ያስቀመጠው ከተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ እና ከክልል ላብራቶሪዎች ጋር በአቅም ግንባታ ሥልጠና፣ በመረጃ ልውውጥ እና በጋራ የአሰሳና ቅኝት እንዲሁም የጥናት ሥራዎችን ሰርቷል ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር ስለመስራት እና ስልጠና ስለመስጠት ሳይሆን የምርምርና ጥናት ሥራዎችን ሲሰሩ የህብረተሰቡን ፍላጎት ያልዳሰሰና የተደረጉት ጥናቶችም ህብረተሰቡ በሚያውቀው ቋንቋ አለመቶርጎሙና ለተጠቃሚዎች አለመሰራጨቱን እንዲሁም ተጠቃሚ አለማድረጉን የሚገልጽ ሲሆን፣ ማእከሉ በአባሪ 33 ግብርና ሚኒስቴር ኢፒዲሞሎጂ ዳይሬክቶሬት ፍላጎቱን ለይቷል ብሎ ያቀረቡት ማስረጃ ቢኖርም የቀረበው ማስረጃ ትክክለኛ ፕሮቶኮሉን ያልጠበቀ ሲሆን የጥናት ሥራዎቹ ያልተሰራጩና ህብረተሰቡ ወደሚያውቁት ቋንቋ ያልተተረጎመ መሆኑ ታውቋል፡፡

86. በመሆኑም ማዕከሉ በተሟላ ሁኔታ የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት አለማድረጉ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲሰራጭ አለመደረጉ ጥናቶቹ የህብረተሰቡን መሰረታዊ ችግሮች ላይ እንዳያተኩሩ እና ህብረተሰቡም የምርምር ውጤቶችን በአግባቡ ወደ ስራ አውሎ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ማዕከሉ የበሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን የሚለይ መሆኑን በተመለከተ

87. ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ሊለይና ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች በማቅረብ በዘርፉ የልማት አጀንዳዎች እንዲቀረጽ ግብዓት የሚሆን መረጃ ማመንጨት ይጠበቅበታል፡፡

88. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች መቅረቡን የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

89. የማዕከሉ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር ሲገናኙ በስብሰባና ስልጠና መልክ ሀሳባቸውን ከማንጸባረቅ ውጪ ሌላ የማሳወቅያ መድረክ ያልተጠቀሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

90. በተጨማሪም በረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ ላይ በተሰጠው መልስ ማእከሉ የበሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮች ከመለየትም በላይ የተለያዩ በሽታዎች አገር አቀፍ የበሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ እንዲቀረጽ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጉልህ ድርሻ አበርክቷል ብለው በአባሪ 04 (MOU AND PPR REPORT) ፣ አባሪ 10፣ (Anti microbial resistance surveillance plan 2019-2023)፣ አባሪ 32 (FMD National control strategy 2017) አባሪ 35 (Anthrax national prevention and control strategy draft, 2017) ሲሆኑ ሁሉም አባሪዎች የተዘጋጁት በግብርና እንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር ሲሆኑ፣ የተገኙት ሰነዶች የመንግስት የሥራ ፕሮቶኮሉን ያልጠበቁ ከመሆኑም በተጨማሪ ማዕከሉ ሥራዎቹን በምን መልኩ እገዛ እንዳደረገ የሚገልጽ ሰነድ አልቀረበም፡፡

91. በመሆኑም የምርመራ ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በህብረተሰቡ ጤና ላይ እና በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ተፅጽኖ የሚያሳድሩ በሽታዎችን በመለየት ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች በማቅረብ በዘርፉ የልማት አጀንዳዎች እንዲቀረጽ ግብዓት የሚሆን መረጃ ማመንጨቱን የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረበ ሲሆን፣ በዘርፉ ለሚታዩ ችግሮች ቀጣይነት ያላቸው ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄዱ ባለማድረግ ዘርፉን በሳይንሳዊ ምርምር ታግዞ እዳያድግ አንዱ ምክንያት ሆነዋል፡፡

## ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ ያለው እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

92. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ እንዲኖር ሊያደርግ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

93. ማእከሉ የላቦራቶሪ ናሙናዎችን የሚያስወግድበት ስርዓት ስታንደርድ ኦፕሬሽን ያለው ቢሆንም ነገር ግን እንደ አገር የናሙና አወጋገድ ስርዓት አስገዳጅ በሆነ መልኩ በፖሊሲ ተቀርጾ በመመሪያ ተደግፎ መውጣት እንደለበት የኦዲት ቡዲኑ ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ ያዘጋጀና ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ ተጠይቆ ማስረጃ አላቀረበም፡፡

94. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፖሊሲ እና መመሪያ የሚያወጣው የግብርና ሚኒስቴር መሆኑን የገለጹ ሲሆን ስለ ሁኔታው የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠይቀው ለእንስሳት በሽታ ለብቻ የጤና ፖሊሲና

መመሪያ ያላወጡ መሆኑን ነገር ግን በግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ውስጥ ማካተታቸውን ገልጸዋል፡፡

95. የማእከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በማዕከሉ የሚሰሩ የምርመራና ምርምር ሥራዎች የተከናወነባቸው ናሙናዎች የሚወገዱበት መመሪያ (Standard Operating Procedure) ያለ መሆኑን በዚሁ መሠረት እየተሰራ የሚገኝ እና በስታንደርድ ኦፕሬሽን ሲስተም መሰረት ደግሞ የላቦራቶሪ ናሙናዎቹ በ120 ድግሪ ሴንት ግሬድ ማቃጠል እንደሚያስፈልግ ይህ ደግሞ በአየር የሚንሳፈፉ ቫይሬሶች ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ነገርግን በተጠቀሰው ልክ ስጋት የሚሆን ነገር የሌለ በመሆኑ ይህንን አጠናቅሮ ለመቀጠል ማዕከሉ ራሱን ገምግሞ የባዬሴፍቲ እና ባዬሴኩሪቲ ስራ ወጥነት ባለው መልክ በማዕከላችንም ሆነ በክልል ላቦራቶሪዎች ለማስቀጠል ከአሜሪካ DTRA PACS ጋር በመሆን የሥልጠናና የዶኩሜንት ዝግጅት ስራ ተከናውኗል ብለዋል፡፡

96. ሆኖም ማዕከሉ በሳይንሳዊ ስታንደርድ ኦፕሬሽን መሰረት ስራዎችን አከናውናለሁ ቢልም ላቦራቶሪው በምስራቅ አፍሪካ ሪፈራል ላቦራቶሪ በመሆኑ ከውጭ ወራሪ ባዮ ሀዛርዶች እንዳይገቡ እና ለሀገራችን ብዝሀ ህይወት ስጋት እንዳይሆኑ እንዲሁም በስታንደርድ ኦፕሬሽን ሲስተሙ መሰረት ደግሞ የላቦራቶሪ ናሙናዎቹ በ120 ድግሪ ሴንት ግሬድ ሲቃጠል በአየር የሚንሳፈፉ ቫይሬሶች ችግር ሊፈጥር ስለሚችል አስገዳጅ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ በማጽደቅ ተግባራዊ ማደረግ አሰፈላጊ ነው፡፡

97. የክልል ላቦራቶሪዎች ባዮሴፍቲ መጠበቅ ላይ በጣም ችግር ያለ (ማለትም በምርመራ ወቅት አፍና አፍንጫቸውን የማይሸፍኑ፣ መስኮት ክፍት መሆኑና የሥራ አከባቢዎቹ ለበሽታ ምርመራ የማይመቹ፣ ቫይሬሶች በአየር ለመንሳፈፍ የሚያግዳቸው የለሌ መሆኑ) በመገኘቱ አንዳንድ በሽታዎች በአየር ላይ በሰዓት 80 ኪሎ ሜትር የሚሄዱ በመኖራቸው (ለአብነትም ኤፍ ኤም ዲ) በአገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያለው እንስሳት በሽተኛ መሆናቸው የላቦራቶሪ ባለ ሙያዎች ይንኑ ለመቆጣጠር የተቸገሩ መሆኑ እና በሳይንሱ መሰረት የታረዱ በሽተኛ እንስሳት የሚቀብሩ ቢሆንም የህግ ከለላ ስለለሌ መቸገራቸው፣ የእንስሳት ወተት ፣ የወተት ተዋጽኦዎች እና ስጋ ህብረተሰቡ ሲጠቀም ለበሽታ እየተጋለጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለወላታ ሶዶ፣ ያቤሎ፣ ህርና፣ ድሬ ደዋ እና ጅግጅጋ ክልላዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

98. በመሆኑም የስታንደርድ ኦፕሬሽን ሲስተሙ እንዳለ ሆኖ የናሙና አወጋገድ ሥርዓት ከሳይንስ ባለፈ ህጋዊ (በአገሪቱ ህግ) ሥር ሆኖ ባለመወጣቱ ወደ አገር የሚመጡት ናሙናዎች የሚያመጡት ተፅጽኖ ማወቅ አልተቻለም፡፡

## ማእከሉ የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት መሰራቱን በተመለከተ

99. ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ያመጡትን ተጸዕኖ በመለየት የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት ሊሰራና እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

100. የማዕከሉ የ basic principles of laboratory biological safety and biosecurity መመሪያ ገጽ 1 በላቦራቶሪው እንዲሁም በአገሪቱ የላቦራቶሪ ናሙና አያያዝ ህይወት ባላቸው ላይ ያመጣቸው ተጽዕኖዎችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

101. ይሁን እንጂ ማእከሉ በማዕከሉም ሆነ በአገሪቱ የላቦራቶሪ ናሙና አያያዝ ያመጣቸውን ተጽዕኖዎች አለመለየቱን ለማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለመጠይቅ ታውቋል፡፡

102. ስለ ጉዳዩ የማእከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ባዮ ሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ጽንሰ-ሀሳቡ የመጣው በቅርብ በመሆኑ ገና እየተማሩ በመሆኑ የሪስክ (የጉዳት መጠን) ልይታ ስራ ያልጀመሩ መሆኑን እንዲሁም የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የባዩሴፍት እና ባዩሴኪሪቲ አሰራር በአገራችን ገና ተግባራዊ አለመደረጉን ገና ስልጠና እየተወሰደ መሆኑን እና የናሽናል ስታንደርድ ወጥቶ እንደ መመሪያ መጽደቅ እንዳለበት ይህንን ስራ ማእከሉ ሀላፊነቱን ወስዶ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፤፤

103. በመሆኑም ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ያመጡትን ተጸዕኖ በመለየት የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት አለመስራቱ እና እርምጃ አለመውሰዱ በላቦራቶሪ ናሙናዎች አማካኝነት በሚከሰቱ በሽታዎች በእንስሳት እና በሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ ይችላል፤

## ማእከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

104. ማዕከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

105. ነገር ግን የማዕከሉ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በሃርድ ኮፒ ወይም ማኑዋል ሲሆን የመረጃ ልውውጡ በላቦራቶሪ ናሙና እና ውጤት ብቻ ሲሆን ከክልላዊ ላቦራቶሪዎች ጋር በአፈጻጸም ሪፖርት እና በጋራ ማቀድ ላይ የማይገናኙ መሆኑ፣ የላቦራቶሪ ናሙና አቀባበል ረጅም ጊዜ የሚወስድ እና በርካታ ባለድርሻ አካላትን (ከገበሬ ጀምሮ ፣ የቀበሌ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የወረዳ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የዞን እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል ላቦራቶሪ እና መጨረሻ ላይ ማዕከሉ የሚደርስ በመሆኑ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ በሚከሰት ወቅት በሽታ በብዛት

እንዲሰራጭ በር የሚከፍት መሆኑ እንዲሁም መረጃዎቹ በኤሌክትሮኒክስ ባለመሆኑ ፍጥነት የለሌው ሲሆን ሁሉም መረጃ ፈላጊ አካል መረጃውን በቀላሉ ለማግኘት እንዳይችል ያደረገ ሲሆን ይህ ሁኔታ እስከ 2010 ዓ.ም የቀጠለ ነገር ግን ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በማዕከሉ ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ ላቦራቶሪ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ መጠቀም የጀመሩ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ከተደረጉ ቃለ-መጠይቆች ታውቋል፡፡

106. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባረዊው ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ማዕከላችን የበሽታ ፍንዳታ ቢከሰትም የተከሰተበት ወረዳ ለክልሉ የእንስሳት ጤና ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል ቢሮውም የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪውን ቦታው ድረስ በመሄድ ጥናት በማድረግ የበሽታውን መንስኤ እንዲለይ ይልካል ብለዋል፡፡

107. የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች የመረጃ ሥርዓቱን ያላዘመኑበትን ምክንያት ተጠይቆ ማዕከሉ የሚሰራቸው ምርመራም ሆነ የምርምር መረጃዎች አለም ዓቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ ተይዞ የሚገኙ መሆኑን አሰራሩም LIMS (Livestock information management system) በሚባል አለም አቀፍ ኤሌክትሮኒክስ ሶፍትዌርን

በመጠቀም የሚሠራ መሆኑን ባለሙያዎቻቸው ይሄንን አስመልክቶ በአሜሪካና በጣሊያን ስልጠና የወሰዱና የሚሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

108. ሆኖም የኦዲት ቡዱኑ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱ የተዘረጋ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የመረጃ ማእከሉን በአካል ምልከታ ባደረገበት ወቅት በ2018 ፣ 125 የምርመራ ናሙናዎችን እንዲሁም በ2019 ፣ 28 የምርመራ ናሙናዎችን መዝግበው የያዙ ሲሆን ነገር ግን የመረጃው ክፍል ሰራተኞች በሥራ ኃላፊዎቹ እንደተባለው በጣሊያንና አሜሪካ ስልጠና ያላገኙ መሆኑን የኦዲት ቡዱኑ ለመረጃ ሠራተኞቹ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የተዘረጋው የመረጃ ስርዓት በማዕከሉ ውስጥ እንጂ ከማዕከሉ ውጭ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ማለትም መረጃው ከኳራንቲኖች ፣ ከገበሬዎች፣ ከክልል ላቦራቶሪዎች እና ከአለም አቀፍ ሪፈር የሚደረጉ ጋር ስለ ናሙናዎች አቀባበልና ስርጭት ስርዓት፣ ስለ በሽታ መረጃ የተገለጸ ነገር የለም፡፡

109. በመሆኑም የላቦራቶሪ መረጃ አያያዙ ከ2011 እንደ ኢትዮጵያን አቆጣጠር ጀምሮ በኤሌክትሮኒክስ የጀመረ ሲሆን ከ2011 በፊት የነበረው በማንዋል መሆኑ፣ ከ2011 በኋላም ቢሆን የመረጃ አያያዙና ልውውጡ ከማእከሉ ውጪ በክልል ላቦራቶሪዎች፣ በኳራንቲኖች፣ እና ሌሎች ባላድርሻ አካላት ጋር በተያያዘ ያልዘመነ ሲሆን በማንዋል በመሆኑ ጊዜ የሚፈጅና የመረጃ ልውውጥ መኖሩ፣ የላቦራቶሪ ናሙና አቀባበል ረጅም ጊዜ የሚወስድ እና በርካታ ተዋናዮችን የሚወስድ (ከገበሬ፣ የቀበሌ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የወረዳ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የዞን እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ የክልል ላቦራቶሪ እና መጨረሻ ላይ ማዕከሉ የሚደርስ

በመሆኑ፣ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ በሚከሰት ወቅት በሽታ በብዛት እንዲሰራጭ በር የሚከፍት መሆኑ እንዲሁም የመረጃ ሂደቱ ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ እንስሳቶቹ እንዲጎዱ ያደርጋል፡፡

## የምርመራ ማዕከሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማመንጨቱን በተመለከተ

110. የምርመራ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት፣ የጉዳት መጠን እና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ሊያመነጭ ይገባል፡፡

111. በደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1፣ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማመንጨት እንዳለበት ይገልጻል፡፡

112. ይሁን እንጂ የምርመራ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት ፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተል እና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ስለ ማመንጨቱ የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ መቅረብ አልቻለም፡፡

113. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት ፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተል እና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ያመነጫል ብለዋል፡፡ ይሄን ይበሉ እንጂ የበሽታ ዓይነትና መገኛው ቦታ፣ የሚያመጡትን የጉዳት ዓይነት ዝርዝር ማስረጃ ፣ የበሽታ ትንተና ሰነዶች ፣ ለያንዳንዱ የበሽታ ዓይነቶች የተነደፉ የቁጥጥር ስትራቴጂዎችን የሚሳይ ሰነድ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

114. በተጨማሪም የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የበሽታ ስርጭት ጥናቶትም ይሁን ቁጥጥሮች በበላይነት የሚመሩት በግብርና ሚኒስቴር እንደሆነ ገልጸዋል፣ ኃላፊው ይሄን ይበሉ እንጂ በወቅቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሠ በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1፣ እንደሚገልጸው ለማዕከሉ ከተሰጡት ተግባራት አንዱ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት ፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማመንጨት መሆኑን ይገልጻል፡፡

115. በመሆኑም ማዕከሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማመንጨት ባለመቻሉ የበሽታ መረጃ ተጠናቅሮ ተንትኖ አልተሰራጨም ፣ አዋጭ የቁጥጥር ሥርዓት ባለመንደፉ ፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ እንስሳት ጤና፣ በቦረና ዞን አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ በደቡብ ክልል እንስሳት ጤና ዳይሬክቶሬት፣ በሉሜ ወረዳ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን እንስሳት ጤና ጽ/ቤት፣ እና በድሬ ደዋ እንስሳት ጤና ጽ/ቤት የእንስሳት ጤና ባለ ድርሻ አካላት የቁጥጥር ሥራ ለመስራት የመረጃ ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ ወቅት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ካቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ችሏል፡፡

## የምርመራ ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

116. የምርመራ ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

117. በደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

118. ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በጅግጅጋና በድሬደዋ ክልል ላቦራቶሪዎች በሁሉም የበሽታ አሰሳና ቅኝት፣ እና የበሽታ ፍንዳታ ምርመራ ፣ ሥራዎች የሚሰሩ ቢሆንም የክልል ላቦራቶሪዎቹ የመረጃ ልውውጥ አድርገው የማያቁ ፣ አብረው የማያቅዱ ፣ ስራቸውን አብረው የማይገመግሙ ፣ መልካም ተሞክሮ እርስ በርስ የማይቀያየሩ እንዲሁም ከማዕከሉ ጋርም በዕቅድና በሪፖርት የማይገናኙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

119. ስለ ጉዳዩ የማእከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር ማዕከሉ የሚገናኝበት ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት አለመኖሩን ነገረግን ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር የሚገናኘው የበሽታ ምርመራ ጥያቄ ሲኖራቸው በስልክ እና በማንዋል /በደብዳቤ/ መሆኑን እንዲሁም የክልል ላቦራቶሪዎች የግንኙነት ስልት አለመንደፋቸውን ገለጸዋል፡፡ በተጨማሪም የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ መግላጫ ላይ በሰጡት መልስ ይህንን አሰራር መዘርጋት ያለበት የግብርና ሚኒስቴር የበሽታ ቁጥጥርና መከላከል የኤፒዲሞሎጂ ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ እያንዳንዱ ክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ የሚሰራው በክልል ከሚገኘው የግብርና ቢሮና የእንስሳት

ጤና ጥበቃ አገለግሎት ጋር በመሆኑ ከማዕከላችን ጋር የሚሰሩት በትብብር መልክ እንጂ የማእከሉ ላቦራቶሪ በኋላፊነት የሚመራቸው አለመሆናቸውን ሆኖም እስካሁን ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር በመሆን ለአገር የሚጠቅሙ ብዙ ስራዎችን መስራታቸውን የደስታ በሽታን ከአገር እስከ ማጥፋት ድረስ አሁንም የበግና ፍየሎች PPR በሽታን ከአገር ለማጥፋት በሚካሄደው የቁጥጥር ስራ በጋራ እየሰራን ነው ብለዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ ኃላፊነቱ የተሰጠው ለማዕከሉ ሲሆን የስራ ዝርዝር ተግባራት ላይም ተገለጸዋል፣ በተጨማሪም ማዕከሉ ከክልል የእንስሳት ላቦራቶሪዎች ጋር እንሰራለን ብለው የመግባቢያ ሰነድ የፈረሙት ሲሆን እነዚህ ስምምነቶች ውስጥ በማዕከሉ ድርሻ ሀገራዊ መረጃ አስተዳደር፣ የክልል ላቦራቶሪዎችን የላቦራቶሪ ጥራትና ሪፖርት መቆጣጠር፣ የክልል ላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣ ችግር ካለበት እርምጃ መውሰድ፣ በክልል ላቦራቶሪዎች የሚገኙ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገናና ካሊብሽን(ልኬት) ያስተባብራል፣ ክልል ላቦራቶሪ ግኝቶች ላይ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ አብሮ ያቅዳል እንዲሁም ለክልል ላቦራቶሪዎች የብቃት ማረጋገጫ እውቅና ይሰጣል ቢልም ማዕከሉ የተዘረዘሩትን ተግባራት መፈጸም ላይ ክፍተቶች አሉ፡፡

120. በመሆኑም ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር በተለያዩ ማለትም በበሽታ ምርመራ ስልት ፣ መልካም ተሞክሮ መጋራት ፣ አብሮ የመስራት ባህል እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ የምርመራ ችግሮች ሁሉ ወደ ማዕከሉ በመምጣት በተሟላ ሁኔታ መልስ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

## ማዕከሉ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን በመሰብሰብ ፤በማጠናቀር እና በሰነድ መልክ የያዘ መሆኑን በተመለከተ

121. ማዕከሉ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ሊሰበስብ ሊያጠናቅር (ሊተነትን) እና በሰነድ መልክ ሊይዝ ይገባል፡፡

122. በማዕከሉ የNational animal health diagnostic and investigation center profile ገፅ 4 ላይ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ይሰበስባል ፤ያጠናቅራል (ይተነትናል) እና በሰነድ መልክ ይይዛል ይላል፡፡

123. ይሁን እንጂ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና መረጃዎችን መሰብሰቡን ፣ ማጠናቀሩን እና ተንትኖ በሰነድ መልክ መያዙን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

124. ስለ ጉዳዩ የማእከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የዚህ ጥያቄ ባለቤት የዋናው መ/ቤት (የግብርና ሚኒስቴር) የበሽታ ቁጥጥርና የኢፒድሞሎጂ ክፍል ሲሆን እኛ ግን ዳታ (መረጃ) ከመስጠት ውጭ የሠራነው ነገር የለም ብለዋል፡፡ ኃላፊው ይሄን ይበሉ እንጂ በማዕከሉ የNational animal health diagnostic and investigation center profile ገፅ 4 ላይ በተቀመጠው መሰረት ማዕከሉ የሀገሪቱን

የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ያጠናቅራል (ይተነትናል) እና በሰነድ መልክ ይይዛል ስለሚል የተሠጠውን መልስ የኦዲት ቡዲኑ መልሱን ለመቀበል ይቸገራል፡፡

125. እንዲሁም ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ማዕከሉ በአለም አቀፍ ደረጃ የ ISO 1725 አክሬዲሽን ዕውቅና ያለውና የሚሰራውም አለም አቀፍ ደረጃውን ተከትሎ መሆኑን የሚሰራቸውንም ሥራዎች ሁሉ በአገር አቀፉ ደረጃ መረጃዎቹ በተገቢው የሚያዙ እና ማንም ሰው ቢመጣ ለማሳየት የምንችለው ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ የኦዲት አባላቱም ከፈለጉ ከSample Reception Unit እና ከማዕከሉ የጥራት ቁጥጥር ክፍል (Quality Management System) በተፈገው ጊዜ ጠይቆ መረዳትና በኤክትሮኒክ መረጃ ቋት ውስጥ ያሉትን ማየትም ይቻላል ብለዋል፡፡ ኃላፊው ይሄን ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ የመረጃ ማዕከሉን በአካል ባየበት ወቅት የነበረው በ2018 ዓ.ም 125 የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት እና በ2019 ዓ.ም የ28 የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ሲሆን ነገር ግን ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም መረጃዎቹ በኤሌክቶኒክስ ያልተያዙ (በማንዋል የተያዙ) ሲሆን የተያዘውም መረጃ ተሰብስቦ በሰነድ መልክ ያልተቀመጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

126. በተጨማሪም የማእከሉ ዋና ዳይሬክተር በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ በ2008 ዓ.ም የእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር በተቋቋመበት ወቅት የተጠቀሰው የሥራ ድርሻ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢፒድሞሎጂ ዳይሬክቶሬት እና ለበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ዳይሬክቶሬት የተሰጠ ነበር ብሏል፣ ነገር ግን በማእከሉ የNational animal health diagnostic and investigation center profile ገፅ 4 ላይ በተቀመጠው እና የማዕከሉ ዳይሬክተርም በመመዘኛ መስፈርት ላይ ከኦዲት ጋር ቡዲኑ በተወያዩት ቃለ-ጉባዔና የመመዘኛ መስፈርት ላይ በሰጡት የመመዘኛ መስፈርት ጽሁፍ መልስ መሰረት ማዕከሉ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ያጠናቅራል (ይተነትናል) እና በሰነድ መልክ ይይዛል ስለሚል የተሠጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

127. በመሆኑም፣ በአገሪቱ ከ2008 ዓ.ም እስከ አሁን ያለው የበሽታ ዓይነት፣ የጉዳት መጠን፣ የሚገኙበት ቦታ፣ በዝርዝር ተተንትኖ ያለ ስለመሆኑ ለማጣራት ማስረጃ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም መረጃዎች ስለመኖራቸው ማስረጃ ወይም ሰነድ ያልቀረበ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በቦረና ዞን፣ በደቡብ ክልል፣ በሉሜ ወረዳ፣ በምስራቅ ሸዋ፣ እና በድሬ ደዋ እንስሳት ጤና ጽ/ቤቶች እንደ አገር የእንስሳት በሽታ መረጃ በማጣታቸው የበሽታ ቁጥጥር ለማድረግ የተቸገሩ መሆናቸው ታውቋል፡፡

**ማእከሉ ሙያዊ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ**

128. ማዕከሉ በወተት ልማት ፣ በኤክስፖርት ቄራዎች እና በደሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል ፡፡

129. በማዕከሉ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትናት (ቢፒአር የጥናት) ሰነድ ገፅ 34 ተ.ቁ 4.4.1 እንደሰፈረው ማዕከሉ በወተት ልማት ፣ በእንስሳት ማድለብ እና በደሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋ ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአለማ ዶሮ ፋርሚስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ፣ በሉና ኤክፖርት ቄራ ድርጅት ፣ በአላና ኤክፖርት ቄራ ድርጅት ፣ በአደአ ወተት ማቀነባበሪያ ህብረት ስራ ማህበር ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሰረት ማእከሉ በበሽታ ዙሪያ እና በምርመራ ዘዴ ስልጠና እና የማማከር ድጋፍ ያልሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

130. የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀ በሰጡት መልስ ለሁሉም የክልል ላቦራቶሪዎች ፣ ለዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች ፣ ተማሪዎች እንዲሁም በወተት ፣ በማር እንዲሁም በከብት ማድለብ ላይ የተሰማሩ ባለ-ሀብቶች ሰራተኞችና ባለሙያዎች እጅግ ሰፊ የጽንሰ-ሀሳብና የተግባር ሥልጠና ሰጥናል ብለዋል፡፡

131. በተጨማሪም የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ማዕከሉ ድጋፍ ለጠየቁ የመንግስትም ሆነ የግል እርባታ ጣቢያዎችን አቅም በፈቀደ መጠን እያገዘ የሚገኝ መሆኑን የእርባታ ጣቢያዎቹም በቅርብ የሚሰሩት ከክልል ግብርና ቢሮዎችና የእንስሳት ጤና ላብራቶሪዎች ጋር ሲሆን ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ከክልል ላቦራቶሪዎች አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝና ድጋፍ ስንጠየቅ እናግዛለን ብለዋል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ በአለማ ዶሮ ፋርሚስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት፣ የሉና ኤክፖርት ቄራ ድርጅት፣ አላና ኤክፖርት ቄራ ድርጅት፣ አደአ ወተት ማቀነባበሪያ ህብረት ሥራ ማህበር እገዛ አድርጎላቸው እንደማያቅና ማእከሉ የእገዛ አገልግሎት መስጠቱን እንኳ አለማወቃቸውን በመግለጻቸው እንዲሁም ስልጠና ሰጥተናል ያሉ ቢሆንም ነገር ግን በዕቅዳቸውም ሆነ በአፈጻጸም ሪፖርታቸው ያልተጠቀሰ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ይቸገራል ፡፡

132. በመሆኑም የአደአ ወተት ማቀነባበሪያ ድርጅት የህብረት ስራ ማህበር ከፍተኛ የእንስሳት ጤና ችግር ያለባቸው መሆኑ ፣ ይህም የማዳቀል ችግር ፤ ጥጆች በሚወለዱበት ጊዜ በብዛት የሚሞቱበት እና አካለ ስንኩላን የሆኑበት ሁኔታ መኖሩ፣ በብዛት የሚወለዱት ጥጆች ወንዶች መሆኑ ፤ይህ ደግሞ እንስሳቶችን ለማራባት አስቸጋሪ እየሆነባቸው መሆኑ እንዲሁም በላሞች ላይ የጡት መደፈን በሽታ የሚከሰትበት ሁኔታ መኖሩ ፣ እንዲሁም በአለማ ዶሮ ፈርሚስ ኃ.የግ.ማ የIB በሽታ

ለመመርመር አቅም አለመፍጠሩ ፣ የደሮ በሽታ በትንፋሽ የሚተላለፊ ስለሆነ ብዙ ዶሮዎችን እየገደለ እና እንቁላል እልዳይጥሉ እያደረገ ከባድ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን በ2010 133,518፣ በ2009 52,549፣ በ2008 51,335፣ በድምሩ 237,402 በሶስት ዓመት ውስጥ IB (infectious bronchitis) ተመርምሮ እርምጃ እንዲወሰድ ባለመደረጉ ከአንድ ድርጅት ብቻ (አለማ ዶሮ ፋርምስ) ዶሮዎች መሞታቸው፣ በመሆኑም በድርጅቱ ሲመረት የነበሩት የዶሮ ዝርያዎች ከበሽታው ጋር ለብዙ ገበሬዎችና አርቢ ድርጅቶች የተሰራጩ በመሆኑ በአገራችን ውስጥ በሽታ ያላቸው ዝርያዎች እንዲስፋፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም ስለመገንባቱ በተመለከተ

133. የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም በመገንባትና በማስተባበር ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ ፣ በበሽታ ቅኝት ፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

134. በወቅቱ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሠ በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 147. የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም በመገንባትና በማስተባበር ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ ፣ በበሽታ ቅኝት ፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ስልጠና ይሰጣል ይላል፡፡

135. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የክልል ከእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በድሬ ደዋ እና በጅግጅጋ ላቦራቶሪዎች ስልጣናዎችን አልፎ አልፎ የሚያገኙ ሲሆን ነገር ግን የሚሰጡ ስልጠናዎች በቂ አለመሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

136. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለክልል እንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች በቂ የጽንሰ-ሀሳብ እና ተግባር ስልጠና እንሰጣቸዋለን ሲሉ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ማዕከላችን ራሱም አቅዶና በክልሎች ጥያቄ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ በማዕከላችን ባለሙያዎችም ሆነ በጋራ በምንሰራቸው አለም አቀፍ ፕሮጀክቶች ባለሙያዎች ልማታዊ የሆኑ የተለያዩ የተግባርና የፅንሰ ሃሳብ ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው ብለዋል፡፡ ነገር ግን የክልል እንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎችም ስልጠና መውሰዳቸውን ያልደበቁ ሲሆን የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ግን ካላቸው ችግር እና ክፍተት አንጻር በቂ እንዳልሆነ ሲገልጹ በተጫማሪም የሚሰጣቸው ስልጠና ዝርዝር ወጥቶ ፣ ታቅዶበት እና ዒላማ ኖሮት የሚሰጣቸው ሳይሆን ከድርጅቶች ስፖንሰር ሲያገኙ የሚያሰለጥኑ መሆኑን እንዲሁም በማዕከሉ ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶች ላይ ለክልላዊ ላቦራቶሪዎች ምን ዓይነት ስልጠና መቼ እንደሚሰጥ ያልታቀደ መሆኑ ፣

ለክልሎች የሚሰጠው ሥልጠና የስልጠና ደሰሳ ጥናት ሳይደረግ ፣ የክልል ላቦራቶሪዎቹ ፍላጎትና ችግር ሳይታወቅ የሚሰጥ መሆኑ፣ እንዲሁም በክልል የአስተዳደር እርከኖች እስከ ወረዳ ባለው የእንስሳት ጤና ዘርፎች በአብዘኛው ሥልጠና ባያገኙም የሚያገኙት በአጋጣሚ ሲሆን ችግሩን መሰረት ያላደገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

137. በተጨማሪም የማዕከሉ ኃላፊ ረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች የራሳቸውን ሆነ በዞን እና በወረዳ የሚገኙትን የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎት ከክልሉ የእንስሳት ጤና ቢሮ ጋር ጋር በመሆን የተለያዩ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በማቀድ ሥራው የሚያስፈልገው በጀት በማስመደብ በመተባበር እና በመገምገም መስራት ያለባቸው እራሳቸው ናቸው ብለዋል፡፡ ነገር ግን የማዕከሉ አንዱ ዋና ሥራ ከሆኑት መካከል የክልል ላቦራቶሪዎችን አቅም መገንባት ስለሆነ አቅም በሚገነባበት ወቅት ዝም ብለው ሥልጠና ከመስጠት ይልቅ ትክክለኛ ችግራቸውን በመለየት ችግሮችን ለመፍታት ማቀድድ ይጠብቅበት ነበር፣ ነገር ግን ይሄንን ሥራዎች ሰርተናል ብለው በአባሪ 43 የክልል ላቦራቶሪዎች ክፍተት አሰሳ ሰርተናል የተባለው የቀረበው ማስረጃ ፕሮቶኮሉን ያልጠበቀ ሲሆን በጥናቱ መሰረትም ወደ ሥራ ያልገቡ በመሆኑ ማስረጃውን ለመቀበል የኦዲት ቡዲኑ ይቸገራል፡፡

138. በመሆኑም የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን ክፍተት በመለየት የእያንዳንዱ የክልል ላቦራቶሪዎች በክፍተታቸው መሰረት እንዲሁም ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የስልጠና ዓይነቶችና የምርመራ ስልት ባለየ መልኩ የክልል ላቦራቶሪዎች አቅም በሚፈለገው አኳኃን ባለመገንባቱ እና እስፔሻላይዝ ባለመደረገቸው አንዱ በሌላ ላቦራቶሪ ዓይነት ሌላኛውን መርዳት ባለመቻሉ ሁሉም የክልል ላቦራቶሪዎች ለአንድ ዓይነት ምርመራ ማዕከሉን በማጣበብ የተሸላ ስራ እንዳይሰራ አደርጓል፡፡

## ማዕከሉ የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱን በተመለከተ

139. ማዕከሉ በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ሊያደርግ እና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡

140. በወቅቱ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርና የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሠ በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1፣ ማዕከሉ በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ሊያደርግ እና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡

141. ይሁን እንጂ ማዕከሉ በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ያላደረገ እና የብቃት ማረጋገጫ ያልሰጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ታውቋል፡፡

142. ስለጉዳዩ የማእከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እስከ አሁን በአገሪቱ የግል እንስሳት ላቦራቶሪ ባለመኖሩ አልሰራንም ሲሉ የማእከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ማዕከላችን ከተሰጡት ተልዕኮዎች ውሰጥ አንዱ የክልል ላባራቶሪዎችን አቅም መገንባት ነው፡፡ በዚህ ረገድ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉንም ክልሎች በቴክኒክ ፣ በግብዓትና በሰው ሀይል ስልጠና ድጋፍ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም የኦዲት ቡዱኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና መርጦ ባያቸው በሉና ኤክስፖርት ቄራ ፣ በአላና ኤክስፖርት ቄራ፣ በአለማ ፋርሚስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፣ የአደአ ወተት ማቀነባበሪያ ህብረት ሥራ ማህበር በድርጅታቸው ውስጥ የራሳቸው የእንስሳት ላቦራቶሪ በመኖሩ እገዛ የሚፈልጉ መሆናቸውን እንዲሁም ለክልል ላቦራቶሪዎቹ እውቅና በመስጠት የብቃት ማረጋገጫ ባለመስጠቱ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች የሰጡትን መልስ የኦዲት ቡዱኑ አልተቀበለም፡፡

143. በተጨማሪም የማእከሉ ኃላፊ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ በአገራችን የላቦራቶሪ የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪድቴሽን ጽ/ቤት እንጂ ማእከሉ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርና የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሠ በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1፣ ማዕከሉ በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ሊያደርግ እና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም በ2001 ከክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረሙ ሲሆን ይህም በማ ዕከሉ ኃላፊነት ሥር ለክልል ላቦራቶሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ መሆኑን ያትታል፡፡

144. በመሆኑም ክልላዊ ላቦራቶሪዎች በተወሰኑ የበሽታ ዓይነት እስፔሻላይዝ አድርገው እንዲሰሩ እውቅና ያልተጠ መሆኑና ክልላዊ የእንስሳት ላብራቶሪዎችን በማብቃትና በማወዳደር ደረጃ የማይሰጥ በመሆኑ አንድ ላበራቶሪ በአንድ የእንስሳት በሽታ ስፔሻላይዝ እንዲያደርግ የህብረተሰቡን የእንስሳት ጤና ችግር ትኩረት ሰጥቶ እንዳይፈታ ያደርጋል፡፡

### ማእከሉ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገናን የሚያካሂድ መሆኑን በተመለከተ

145. የምርመራ ማዕከሉ በከፍተኛ ወጪ፣ በውጭ ምንዛሪ እየተገዙ የሚመጡ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አስተዳደር እንደዚሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ሊገነባና ለክልል ላቦራቶሪዎች ድጋፍ ሊሠጥ ይገባል፡፡

146. በወቅቱ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርና የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሠ በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1 157. የምርመራ ማዕከሉ በከፍተኛ ወጪ ፣ በውጭ ምንዛሪ እየተገዙ የሚመጡ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም እንደሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ሊገነባና ለክልል ላቦራቶሪዎች ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለው ይገልጻል፡

147. ይሁን እንጂ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አስተዳደር እንደዚሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ያልገነባ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተለያዩ ሰነዶች፣ ከክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችና ከማእከሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ከተደረገው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

148. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይሄንን ተግባር በተወሰነ መልኩ እንዲጠግኑ ለማድረግ በአገር ውስጥ የተማሩ በአሁን ጊዜ እየሰሩ ያሉ ባለሙያዎች ያሉዋቸው መሆኑን እና አቅማቸው በፈቀደ መጠን የማዕከላችንንም ሆነ የክልል ላቦራቶሪዎች መሳሪያዎች ብልሽት ባጋጠማቸው ጊዜ የጥገና አገልግሎት እንደሚሰጡ ሆኖም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚመጡ የበሽታ መመርመሪያ ኢክውፕመንቶች እጅግ ሶፌስትከትድ (የረቀቁ) በመሆኑ የኛ ባለሙያዎች ሊጠግኑዋቸው ስለማይችሉ በውጭ ቴክኒሻኖች የሚጠገንበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

149. እንዲሁም የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በአገራችን በአጠቃላይ በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከልም ይሁን በክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችና በሰው ሆስፒታሎችና ላቦራቶሪዎች የሚገኙ መሳሪያዎችን በተበላሹ ግዜ የሚጠግን የሰው ሀይልም ይሁን ዎርክሸፕ መጠገኛ ገና አልተገነባም ብለዋል፡፡

150. በመሆኑም የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም እንደሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ያልገነባ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ማዕከሉ በሌላ አካል የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ለማስጠገን እና ለመለካት ወይም ካሊብሬት ለማድረግ ከ2008-2010 ዓ.ም አንድ መቶ ሰማኒያ አራት ሺህ አምስት መቶ ስድሳ ሁለት ብር ከሀያ ዘጠኝ ሳንቲም ወጪ እንዲያደርግ ያደረገ ሲሆን ሌሎች በክልል የሚገኙ ላቦራቶሪዎች መሳሪያዎች በጥገና ምክንያትና በባለሙያዎች አቅም ውስንነት ምክንያት የላብራቶሪ መሳሪያዎች ስራ ውጭ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

151. ለዓብነት የወላይታ ሶዶ ቀጠና የእንስሳት ጤና ላባረቶሪ ውስጥ ያሉ መሳሪያዎች ተበላሽተው የሚጠግናቸው ባለሙያ ባለመኖሩ እንዲሁም አዲስ የተገዙ መሳሪያዎች አገልግሎት የማይሰጡ centrifuge, autoclave,water bath,microtone, tissue processor,block holder frige ሲኖሩ፣ በሂርና ላብራቶሪ ብዙ መሳሪያዎች በጥገና ምክንያት ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡበት ሁኔታ መኖሩ ፣ ከእነዚህም ውስጥ elize reader, safety cabinet, supra speed centrifuge, desk top centrifuge, computerized centrifuge, autoclave, autoclave manual, biological incubator, co2 incubator ሲሆኑ፣ እንዲሁም ደግሞ በባለሙያ አቅም ማነስ ምክንያት የማይጠቀሙባቸው መሳሪያዎች እንደ spectro photometer and lyophilize እንዲኖሩ አድርጓል፡፡

## ማዕከሉ የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን ማጎልበቱን በተመለከተ

152. ማዕከሉ የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን ሊያጎለብት ይገባል፡፡

153. በማዕከሉ የ2ተኛው የተከለሰው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ገጽ 4 የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን እንደሚያጎለብት ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ማዕከሉ በኤክስፖርት ቄራዎች እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅም ለማጎልበት የተሰራ ስራ አለመኖሩን በናሙና ተመርጠ በታዩት ለድሬደዋ እና አዳማ ኳራንቲኖች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የበሽታ ምርመራ እገዛ ተደርጎላቸው የማያውቅ መሆኑን እንዲሁም በሉና እና ላና ሥጋ ኤክስፖርት ቄራዎች በስልጠናም ይሁን በሙያዊ ምክር ምንም ዓይነት ዕገዛ ተደረጎላቸው የማያቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

154. ስለ ጉዳዩ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ይሄ ስራ የሚመለከተው በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው የወተትና ሥጋ ልማት ኢኒስቲትዮትን እንጂ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማእከልን አለመሆኑን ገልጸው ምክንያቱን ሲያብራሩ ኤክስፖርት ቄራዎችን የሚከታተሉት እነሱ ሲሆኑ ነገር ግን ኳራንቲንን በተመለከተ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴው የሚመራው በግብርና ሚኒስቴር የኳራንቲን ዳይሬክቶሬት ነው ብለዋል፡፡ ኃላፊው ይሄን ይበሉ እንጂ የሥጋና ወተት እንዱስትሪ ልማት እንስቲትዩት የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪን የማይከታተል ሲሆን እንዲሁም ኳራቲንን በተመለከተም አጠቃላይ የስራ ሁኔታውን

ሳይሆን በኳራንቲኑ ውስጥ የሚገኘውን የእንስሳት ላቦራቶሪ እንዲጠናከር የሚሰራው ማዕከሉ በመሆኑና ማዕከሉም ይሄንን ሥራ መስራት ሲገባው ያልሰራ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለም፡፡

155. በተጨማሪም ኃላፊው በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት መልስ በሚሌ እንስሳት ኳራንቲን እና በአልፎዝ እንተርናሽናል ኳራንቲን ላቦራቶሪ በሙያም ሆነ በተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች እገዛ ማድረጋቸውን የገለጹ ሲሆን ነገር ግን በናሙና ተመርጠ በታዩት ኳራንቲኖችና የስጋ ላኪ ድርጅቶች እገዛ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡

156. በመሆኑም የሥጋ ኤክስፖርት ቄራዎቹ፣ የእንስሳት ጤና ምርመራ አቅም አለማደጉና በአገራችን የእንስሳት በሽታዎች ሥጋት ስላለ በላቀ ደረጃ ምርመራ አድርጎ ከሥጋት ነጻ መሆን እንዳይቻል አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥና የአቅም ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል እና በናሙና ተመርጠው በታዩት የክልል እንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪዎች፣ እንስሳት ጤና ጽህፈት ቤቶችና ቢሮዎች፣ እንዲሁም ኳራንቲኖች የታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

157. በአገር ደረጃ የእንስሳት የጤና ፖሊሲ የሌለ ሲሆን ማዕከሉም የመተዳደሪያ ደንብ ቢያዘጋጅም ጸድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጫማሪ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ ወይም መመሪያ ባለመኖሩ በአገራችን በተለያየ አከባቢ የሚገኙ እንስሳቶች ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የተጋለጡ መሆናቸው የታወቀ መሆኑ እንዲሁም ማዕከሉ ከሚያከናዉናቸዉ ተግባሮች አኳያ የፀደቀ የተቋቋመበት ደንብ ስለሌለዉ፣ ህጋዊ የስራ ድርሻዉን በግልፅ የሚያስቀምጥ ሰነድ አለመኖሩ፣

158. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሄ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በወቅቱና በአፋጣኝ በመለየት ለተገልጋዮች በሚጠበቀው ደረጃ የተሟላ መፍትሔ ያልሰጠ መሆኑ፤

159. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራን ውጤት ከውስጣዊና ውጫዊ ተዕጽኖዎች ሊጠብቅ የሚያስችል ብቃት ያለው የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት በሚጠበቀው ደረጃ ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

160. ማእከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፣

161. ማዕከሉ በኦፕሬሽናል ማንዋሉ መሰረት የበሽታ አሰሳዎችን (በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ በሶስት ዓመት አስራ ሁለት ጊዜ) በተሟላ ሁኔታ የበሽታ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፣

162. ማዕከሉ ከዚህ በፊት በምርመራው ከሚታወቀው ሁለት የምርመራ ዓይነት ማለትም አቭያን እንፍሉዌኔዛና ኒውካስትል እውቅና ያገኘ ሲሆን በሌላ የበሽታ ዓይነቶች እውቅና ያላገኘ መሆኑ፣

163. ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን በተሟላ ሁኔታ የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት አለማድረጉ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደ ሚያውቁት ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲሰራጭ አለመደረጉ፣

164. የምርመራ ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በህብረተሰቡ ጤና ላይ እና በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ተዕጽኖ የሚያሳድሩ በሽታዎችን በመለየት ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች

በማቅረብ በዘርፉ የልማት አጀንዳዎች እንዲቀረጽ ግብዓት የሚሆን መረጃ ስለማመንጨቱ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

165. ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ያመጡትን ተጽዕኖ በመለየት የባዮሴፍቲ እና ባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት ያልሰራ መሆኑ፣

166. ማዕከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም እስከ 2010 ዓ.ም በማንዋል መሆኑ፣

167. ማዕከሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ስለማመንጨቱ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበና የበሽታ መረጃ ተጠናቅሮ እና ተንትኖ ያልተሰራጨ መሆኑ፣

168. በአገሪቱ ከ2008 ዓ.ም እስከ አሁን ያለው የበሽታ ዓይነት፣ የጉዳት መጠን፣ የሚገኙበት ቦታ፣ በዝርዝር ተተንትኖ ያልተያዘ መሆኑ፣

169. ማዕከሉ በወተት ልማት ፣ በኤክስፖርት ቄራዎች እና በደሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች በቂ ሙያዊ ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣

170. የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን ክፍተት በመለየት የእያንዳንዱ የክልል ላቦራቶሪዎች በክፍተታቸው መሰረት እንዲሁም ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የስልጠና ዓይነቶችና የምርመራ ስልት በመለየት፣ በእቅድ ይዞ፣ ስልጠናዎችን የማይሰጥ መሆኑ፣

171. ማዕከሉ የክልል ላቦራቶሪዎችን በተወሰኑ የበሽታ ዓይነት እስፔሻላይዝ አድርገው እንዲሰሩ እውቅና ያልተጠ መሆኑ፣

172. የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አስተዳደር እንደሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ያልገነባ መሆኑ፣

173. ማዕከሉ የኤክስፖርት ቄራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን በተሟላ ሁኔታ የመመርመር አቅማቸውን ያላጎለበተ መሆኑ፣

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

174. እንደ ሥራ ተግባርም ሆነ እንደ ሙያ ማዕከሉ ከፍተኛ ኃላፊነት እና የሙያው እውቀት እንዲሁም በእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ዙሪያ ያሉትን የበሽታ ቁጥጥር ችግሮች በቅርበት የሚያውቁ በመሆኑ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን (የእንስሳት ጤና ፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማርቀቅ)፣ እንዲሁም አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ፣ ሊያሳምን፣ ሊያጸድቅ እና ሲፀድቅም ተግባራዊ ሊያደርግ ይጠበቅበታል፡፡
175. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሔ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች በባለድርሻ አካላት ወይም አገልግሎት ፈላጊ ህብረተሰብ (ገበሬዎች፣ እንስሳት አርቢ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣ የመንግስት የአስተዳደር እርከኖች፣ እና የክልል ላቦራቶሪዎች) መረጃው ሲደርስ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በመለየት ለተገልጋይ በወቅቱ የመፍትሔ ሀሳብ በማቅረብ፣ የእንስሳት ሞትና የበሽታውን መስፋፋት ሊቀንስ እንዲሁም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ሊያሳድግ ይገባል፡፡
176. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር አስተዳደር 1725 (ISO/IEC17025:2005, WI-GEN-001 Issue no, 1A) ስርዓት ያለው ቢሆንም ተግባራዊ ማድረግ ላይ ግን ክፍተቶች በመኖራቸው በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግና በዚሁ መሰረት ወደ ውጭ የሚላኩት የቁም እንስሳትን በተመለከተ የማዕከሉ ባለሙያዎች ከላኪ ድርጅቶች ጋር ሂዶ ናሙና መቅዳትን በማቆም በኳራንቲኖችና በግል ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የእንስሳት ላቦራቶሪዎችን በማጎልበት የምርመራ ናሙና እንዲያመጡ ሊያደርግ ይጠበቅበታል፡፡
177. ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ለመስጠት አከናውናለው ብሎ ከ2008-2012 ዓ.ም ያስቀመጠውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፣
178. ማዕከሉ በኦፕሬሽናል ማንዋሉ መሰረት በአገሪቱ የበሽታ አሰሳና ቅኝት በማድረግ የበሽታ መረጃዎችን ሊሰበስብ ይገባል፡፡
179. ማዕከሉ  አስፈላጊውን መሳሪያዎች በማደራጀት እና አስፈላጊውን የሰው ሀብት በማብቃት እንዲሁም ጥብቅ የእንስሳት ላቦራቶሪ ምርመራ  ህጋጋትን በመከተል ተዓማኒነቱ የተረጋገጠ የላቦራቶሪ ውጤት በማቅረብ  ዕውቅና ለማግኘት ሊያቅድ፣ሊሰራና በሽታ ቁጥጥር ውስጥ ጉልህ ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡

180. ማዕከሉ የበሽታ ጥናት ሲያከናውን የህዝቡን ችግርና ፈላጎት የዳሰሳ ጥናት በመስራት ሊረዳ፣ በደሰሳ ጥናቱ መሰረት አንገብጋቢ የሆኑ የህብረተሰብ የእንስሳት ጤና ችግሮችን በማጤን መረጃ በማመንጨት እና ህብረተሰቡ ወደሚያውቀው ቋንቋ ተቶርጉሞ ሊሰራጭ ይገባል፡፡

181. ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ልዩ ተኩረት በስጠት በህብረተሰቡ ጤና ላይ እና በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ተዕጽኖ የሚያሳድሩ በሽታዎችን በመለየት ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ከሙያዊ ምክረ-ሀሳብ ጋር ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች ማቅረብና መፍትሄ እንዲበጅለት ሊያደርግ ይኖርበታል፡፡

182. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ አዘጋጅቶ በማጽደቅ ህጋዊ ሰውነት እንዲኖረው ማድረግና ተግባራዊ ሊያደርግ ይጠበቅበታል፡፡

183. ማዕከሉ በራሱ ላቦራቶሪ እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ሊያመጡ የችሉትን ችግሮችን ለመከላከል የላቦራቶሪ ባዮሴፍቲ እንዲተገብር ሊያደርግና ተግባራዊነቱን በጥብቅ ሊከታተል እንዲሁም የላቦራቶሪ ናሙናዎቹ ያመጣቸውን ተጽዕኖዎች በመለየት የባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት ሰርቶ የመፍትሄ ሀሳብ ሊያቀርብ ወይም ከአቅሙ በላይ ከሆነ የሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስድ ሪፖርት ማድረግ ይገባል፡፡

184. በማዕከሉ የላቦራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ጥሩ ጅማሮዎች ያሉ ቢሆንም የተዘረጋው ሥርዓት በላቦራቶሪው ውስጥ ብቻ በመሆኑ ከላቦራቶሪ ውጭ ባሉት ከክልል ወደ ማእከሉ ያሉት የመረጃ ልውውጦች በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ በመጠቀም የመረጃ ልውውጡን ሊያፋጥን ይጠበቅበታል፡፡

185. የምርመራ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን የት አከባቢ በሽታዎች እንዳሉ በመለየት፣ የተገኙበት የእንስሳት ዓይነት፣ የሥርጭት መጠን፣ ሊያደርሱ የሚችሉ የኢኮኖሚ ተዕጽኖ በመዘርዝር እና ሌሎች መረጃዎች በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ሊያመነጭ ይገባል፡፡

186. የምርመራ ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ከክልል ላቦራቶሪዎች ጋር በዕቅድ፣ በሪፖርት እና በግምገማ እንዲሁም አብሮ በመስራት ላይ መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ሊሰራ ይገባል፡፡

187. ማዕከሉ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን በሰነድ መልክ ሊይዝ እና መረጃውን ለመረጃ ፈላጊዎች ሁሉ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

188. ማዕከሉ በወተት ልማት፣ በኤክስፖርት ቄራዎች፣ እና በዶሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች በእንስሳት ጤና ምርመራ ለባለሙያዎቻቸው ሙያዊ ድጋፍ ሊይደርግ ይገባል፡፡

189. የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም ለመገንባት የሚያስፈልጉ ድጋፎችን አሰሳ በማድረግ መለየት፣ እንዴት አቅማቸውን እንደሚያጎለብቱ በማቀድ፣ እና በመተግበር ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ፣ በበሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና በመስጠት የክልል እንስሳት ላቦራቶሪዎችን ደረጃቸውን በመለየት እውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

190. የምርመራ ማዕከሉ በከፍተኛ ወጪ፣ በውጭ ምንዛሪ ተግዝተው የሚመጡ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች ላይ ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል የአጭር እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት የማዕከሉን የቴክኒክ ብቃት በመገንባት እና ያሉትን መሳሪዎች በመጠገን እና የላቦራቶሪ ማሳሪያዎችን ለመጠገን የሚወጣውን ወጪ ሊያድን እንዲሁም የክልል ላቦራቶሪዎችን በማሰልጠን በጥገና ሥራ አቅማቸውን ሊገነባ ይገባል፡፡

## አባሪ 1

### መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

**የኦዲት አከባቢ፣ -** <u>የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥ እና የአቅም ግንባታ አፈጻጸምን መገምገም፤</u>

| የኦዲት ጭብጥ (Issues) | የመገምገሚያ መስፈርት (Evaluative criteria) |
| --- | --- |
| 1. ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ማዕከል የሚያከናውናቸው የእንስሳት ጤና ምርመራ ፣ የእንስሳት በሽታ አሰሳና ቅኝት እንዲሁም የጥናት ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም፣ | 1. ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን ፣ አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሊያቀርብ እና ሲፀድቅም ሥራ ላይ ሊያወል ይገባል፡፡ <br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1ገጽ4** |
| | 2. የምርመራ ማዕከሉ አገራዊ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ሥራዎችን ለመተግበር የሚያስችል የፕሮጀክት ሰነድ ሊያዘጋጅና በሚመለከታቸው ሁሉ ተግባራዊ እንዲደረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡ <br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር** |

| | |
|---|---|
| | **በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/**አው**2/1/1**ገጽ**4 |
| | 3. የምርመራ ማዕከሉ የበሽታ አሰሳና ቅኝት የናሙና መረጃ አሰባሰብ መመሪያ ወይም ማኑዋል ሊያዘጋጅ ይገባዋል፡፡ <br> **ምንጭ፡- ቢፐአር የጥናት ሰነድ ገፅ**22 **ተ.ቁ** 1.11 |
| | 4. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሔ የሚሹ የእንስሳት ጤና ቸግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በመለየት ለተገልጋይ በወቅቱ የመፍትሔ ሀሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡- ቢፐአር የጥናት ሰነድ ገፅ**11 |
| | 5. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራን ውጤት ሊያስቀይሩ የሚችሉና አስተዳደሩን እና ባለሙያዎችን ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ሊጠብቅ የሚችል የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡-** ISO/IEC17025:2005, WI-GEN-001 Issue no, 1A |
| | 6. ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡- ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል** 2**ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ገጽ** 5 |
| | 7. ማዕከሉ የበሽታዎች ምርመራና አሰሳ በማካሄድ ወቅታዊ ምርመራ ሊያካሂድ ይገባል፡፡ <br> **ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/**አው**2/1/1 |
| | 8. ማዕከሉ ከአገር ለሚወጡና ወደ አገር ለሚገቡ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽያዎች |

| | |
|---|---|
| | ውጤታማ እና ተዓማኒነት ያለው የበሽታዎች ምርመራ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/እው2/1/1** |
| | 9. ማዕከሉ የማዕከሉን የምርመራ ቴክኒክና የሥራ ሂደት ብቃትን በይበልጥ በማጎልበት ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እና ተቀባይነት ያለው ላቦራቶሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/እው2/1/1ገጽ3** |
| | 10.ማዕከሉ የምርመራ መሳሪያዎችን በወቅቱ ካሊብሬት ሊያደርግ /ሊለካ/ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ ቢፒአር የጥናት ሰነድ ገፅ 30 ተ.ቁ 4.1.9** |
| | 11.የምርመራ ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ጥናት ሲያከናውን የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መሰረት ሊያደርግ እንዲሁም የምርምር ውጤቶቹ ተጠቃሚዎች ወደሚያውቁት ቋንቋ ተቶርጉሞ ሊሰራጭ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 12.ማዕከሉ የእንስሳት በሽታ ምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለምርምርና ለልማት የሚሆኑ ጉዳዮችን ሊለይና ለሚመለከታቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች ሊያቀርበ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/እው2/1/1ገጽ4** |
| 2. የምርመራ ማዕከሉ ውጤታማ የባዮ ሴኪዩሪቲና ባዮ ሴፍቲ ሥርዓት መዘርጋቱንና | 13. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ እና መመሪያ እንዲኖር ሊያደርግ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| የአፈጻጸሙን ውጤታማነት መገምገም፤ | **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 14.ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙና ያመጣቸው ተጸዕኖ በመለየት የባዮሴኪዩሪቲ ሪስክ አሰስመንት ሊሰራና እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** basic principles of laboratory biological safety and biosecurity, page 1 |
| | 15. ማዕከሉ በላቦራቶሪው እና በአገሪቱ ውስጥ የላቦራቶሪ ናሙና ያመጣቸው ተጸዕኖ በመለየት የባዮ ሴፍቲ ሪስክ አሰስመንት ሊሰራና እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** basic principles of laboratory biological safety and biosecurity, page1-5 |
| 3. የምርመራ ማዕከሉ ለመረጃ አያያዝ እና ሥርጭት ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 16.ማዕከሉ የላብራቶሪ መረጃ አያያዝ እና ሰርጭት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br><br>ምንጭ፡- ቢፕአር የጥናት ሰነድ ገፅ 32 ተ.ቁ 24.1.27 |
| | 17.የምርመራ ማዕከሉ ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርሱ የእንስሳት በሽታዎች ስርጭት፣ የጉዳት መጠንና መሰል መረጃዎችን በማሰባሰብ የበሽታ ቅደም ተከተልና አዋጪ የቁጥጥር ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ሊያመነጭ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/አው2/1/1 |
| | 18.የምርመራ ማዕከሉ በክልል ላቦራቶሪዎች መካከል የሚኖረው የመረጃ ልውውጥ ዘመናዊ እና የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል አንድ ወጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ** |

| | |
|---|---|
| | **እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/እው2/1/1 |
| | 19.ማዕከሉ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ሊሰበስብ ፤ሊያጠናክር (ሊተነትን) እና በሰነድ መልክ ሊይዝ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** National animal health diagnostic and investigation center profile **ገፅ** 4 |
| 4. ማዕከሉ ከተገልጋዮች እና ባለ-ድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርና ለተገልጋዮቹ የሚሰጣቸው የአቅም ግንባታ እና የክትትል ሥራዎች ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ፡ | 20.ማዕከሉ በወተት ልማት፣ እና በደሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል ፡፡ **ምንጭ፡- ቢፒአር የጥናት ሰነድ ገፅ** 34 **ተ.ቁ** 4.4.1 |
| | 21.የምርመራ ማዕከሉ የክልል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን አቅም በመገንባትና በማስተባበር ለክልል እንስሳት ጤና የመስክና የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ቴክኒክ፣ በበሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና ለሰጥ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/እው2/1/1 |
| | 22.ማዕከሉ በግል ለሚቋቋሙና በክልሎች ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች አንድ ወጥ የላቦራቶሪ በሽታ ምርመራ እንዲኖር ሊያደርግ እና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር** 15/እው2/1/1 |
| | 23.የምርመራ ማዕከሉ በከፍተኛ ወጪ፣ በውጭ ምንዛሪ እየተገዙ የሚመጡ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም፣ እንደዚሁም ብልሽት ሲደርስ ጥገና ማድረግ የሚያስችል አቅም ሊገነባና ለክልል ላቦራቶሪዎች |

| | |
|---|---|
| | ድጋፍ ሊሠጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር በማዕከሉ እንዲተገብር የተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር 15/አው2/1/1** |
| | 24.ማዕከሉ የኤክስፖርት ቁራዎችን እና በኳራንታይኖች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን የመመርመር አቅማቸውን ሊያጎለብት ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- 2ተኛው የተከለሰው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅ ገጽ 4** |